


ዋጋው አንድ ብር

በአክሱም የሚገኘው ሐውልት

# ትንሣኤ



የአክሱም ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፳፬

ኅዳር ፲፱፻፷፮ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጥምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሉ ተሰይሟል ። »

አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም በለጠ አበበ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማ ው ጫ

## አርእስት ፤ ገጽ

ደብዳቤዎች . . . . . . . . . ፩
በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል . . . ፪
እናታችን ጽዮን . . . . . . . ፬
ወደ ሀገርህ ተመለስ . . . . . . ፮
አቡነ ጳንጠሌዎን . . . . . . . ፯
ልማት በቤተ ክርስቲያን . . . . . ፰
ነነብያት ጾም . . . . . . . . ፲
የክርስቲያን አምላክ ሰው ሆኖ መጣ . . . . ፲፩
ዜና ሊቃውንት . . . . . . . ፲፫
ከኢትዮጵያን ቅዱሳን ታሪክ . . . . . ፲፬
ቅድስት ሐና . . . . . . . . ፲፭
የተቀደሰ ጋብቻ . . . . . . . ፲፯
ዜና እረፍት . . . . . . . . ፲፰
የወባ በሽታ መከላከያ . . . . . . ፳
የግብርና በረከት . . . . . . . ፳፩
የባህል አምድ . . . . . . . . ፳፪
ሰባኪያንና ስራቸው . . . . . . .

## ደብዳቤዎች

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ ፤
አዲስ አበባ

1/ በሐዋርያት ሥራ ም. ፰ ቁ. ፳፮ ጀምሮ የሚነገረውና ፊልጶስ ያጠመቀው ጥምቀትን ወደ ኢትዮጵያ አመጣ የሚባለው የኢትዮጵያ ንግሥት ሕንደኬ ጃንደረባ መጠሪያ ስሙ ማን ይባላል ?

2/ አፄ ላሊበላ ያሠራቸው አብያተ ክርስቲያናት በስንት ዓመተ ምህረት ተጀምረው በስንት ዓመተ ምህረት ተፈጸሙ? በስራውስ እነማን ይረዱት ነበር ?

እነዚህ ጥያቄዎች በትንሣኤ መጽሔት አማካይነት ተብራርተው ይገለጹልኝ የመጽሔታችሁ ተከታታይ ።

ተማሪ ሶስና ጴጥሮስ

። ። ።። ከሐረር ።

ተማሪ ሶስና ጴጥሮስ መጽሔታችንን እየተከታተልሽ ስለምታነቢ እናመሰግንሻለን ወደፊትም መጽሔታችንን እየተከታተልሽ በማንበብ ጥያቄዎችን ብታቀርቢልን የተብራራ መልስ ለመስጠት ዝግጁዎች መሆናችንን በደስታ እንገልጽልሻለን ።

በአንደኛው ጥያቄሽ ላይ የአቀረብሽው የሕንደኬ ጃንደረባ መጠሪያ ስሙ ማን ይባል ነበር ለሚለው የጃንደረባው ስም ሰባኮስ ይባላል ።

በሁለተኛው ጥያቄሽ ደግሞ አፄ ላሊበላ የአብያተ ክርስቲያናቱን ሕንፃ በስንት ዓ.ም. ጀምሮ በስንት ዓ.ም. ፈፀመው ለሚለው ዓፄ ላሊበላ ከቋጥኝ ተፈልፍለው የታነፁትን የአስራ አንዱን አብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ ሥራ የጀመረው ፩ሺ ፩፻፹፩ ዓ.ም. ሲሆን ፳፫ ዓመት ከፈጁ በኋላ በ፲፪፻፬ ዓ.ም. ተጠናቀቀ እየተባለ ይነገራል ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች ደግሞ በ፩ሺ ፪፻፰ ዓ.ም. ተጠናቀቀ እያሉ ይናገራሉ ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች ደግሞ ሥራቸው የፈጀው ፳ ዓመት ብቻ ነው ይላሉ አብዛኞዎቹ ግን የሚደግፉት ፳፫ ዓመት ፈጀ የሚለውን ነው።

ላሊበላ ሕንፃውን በሠራ ጊዜ የረዱት እነማን ናቸው ? ለሚለው አብዛኞዎቹ የኢትዮጵያ ጠበብት ሲሆኑ አልፎ አልፎም የግብፅ ስደተኞች እንደነበሩበት ይነገራል ። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን ለዚህ ሕንፃ ዋና ሠራተኞች መሆናቸውን የሚያረጋግጠው ይህንን ሕንፃ የመሰለ በኢትዮጵያ በአንዳንድ ክፍላተ ሀገራት በብዛት ተሠርቶ ስለሚገኝ ነው።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ ፤

በቅድሚያ ሥራችሁ የተቃና እንዲሆን እንመኛለን እኛም ለመጽሔቱ ደንበኞች (ተከታታዮች) በመሆን ትንሣኤ መጽሔት በሚያወጣው መንፈሳዊ ትምህርት እንካፈላለን አሁንም ልንጠይቅ የፈለግነው ጥያቄ አለን ። ይኸውም፩ኛ/ ወንጌል መጀመሪያ የተጻፈበት አገር ማን ይባላል ? በምንስ ቋንቋ ተጻፈ ? የተጻፈበትስ ምክንያት ለምን ነበር ?።

፪ኛ/ ወንጌሎቹ የተጻፉበት ዘመን በየትኛው ዓ/ም ነበር ? ደግሞስ ጌታ በሚያስተምርበት ጊዜ ከእርሱ ጋር እየተከታተሉ የሚያስተምረውን ነው የጻፉት? ወይስ በመንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው ነው ?

፫ኛ/ ወንጌል የተጻፈው ጌታችን ባረገ በስንተኛው ዓመት ነው ? አራተኛውን ወንጌልስ የጻፈው ማን ነበር ?

ከአንዳንድ ሰዎች እንደምንሰማው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው ሉቃስ ወንጌላዊው ነው ። የጻፈው በማለት ይናገራሉ በቂ መልስ ለማግኘት ባለመቻላችን ፤ ከሰዎች ለሚቀርበው ጥያቄም ሆነ ክርክር ወሣኝነቱ ጠይቆ መረዳት መሆኑን ስለአመንበት በእናንተ ዘንድ ጥያቄው ታይቶልን ተብራርቶ በትንሣኤ መጽሔት እንዲረጋገጥልን በናፍቆትና በጉጉት እንጠባበቃለን ።

የመጽሔቱ አፍቃሪዎች ወ/ት አበበች ዓለሙ ም/የ፲ አለቃ ሰሎሞን ዓለሙ

አ.አ. ፤

ጠያቂዎች ለአቀረባችሁት ጥያቄ መልስ ከመስጠታችን አስቀድሞ የጥያቄአችሁ አቀራረብ ራስን ለማስተማርም ሆነ ሌላውን ለማሳወቅ የቀረበ ጥያቄ መስሎ ስለታየን እናመሰግናለን ።

በመሠረቱ ወንጌል አራት ክፍሉና ተጽፋለች ፤ ጸሐፊዎቹም አራት ናቸው ። እነዚህም ሁለቱ ከሰባ አርድዕት ማርቆስና ሉቃስ ሲሆኑ ሁለቱ ማቴዎስና ዮሐንስ ደግሞ ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ናቸው ።

በጥያቄአችሁ ላይ አራተኛውን ወንጌል የጻፈው ማን ነው ይላል ። መልሱም በማያጠራጥር መንገድ የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ ነው ። እርሱ ለመሆኑም በዚሁ ወንጌል ላይ ይህንንም ጽፎ ያለ ይህ ደቀመዝሙር ነው ። ምስክሩም እውነት እንደሆነ እናውቃለን ። ሲል እናገኘዋለን ። ዮሐ ፳፩ ቁ ፳፬ ።

፪ኛ/ ወንጌል በመጀመሪያ በየት አገር በምን ቋንቋ በስንት ዓ/ም ተጻፈ ለሚለው ጥያቄ በመጀመሪያ ማቴዎስ በፍልስጥኤም አገር በዕብራይስጥ ቋንቋ ጌታ ባረገ በ፰ኛው ዓመት ተፈጽሞ ፱ኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በመጀመሪያው ዓመት በህንድ ጽፎ ጨርሶታል ።

፫ኛ ማርቆስ በሮም በሮማይስጥ ቋንቋ ጌታ ባረገ በ፲፩ኛው ዓመት ተፈጽሞ ፲፪ኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በአራት ዓመት በ፵፰ ዓ.ም. ጽፏል ።

፬ኛ/ ሉቃስ በጽርዕ አጠገብ በምትገኝ በመቄዶንያ ሀገር በዮናኒ ቋንቋ ጌታ ባረገ በ፳፩ኛው ዓመት ተፈጽሞ ፳፪ኛው ሲጀመር ቀላውዴዎስ ቄሣር በነገሠ በ፲፬ ዓመት በ፶፰ ዓ/ም ጽፏል ።

፭ኛ/ ዮሐንስ በኤፌሶን (ግሪክ) በዮናኒ ቋንቋ ዮሐንስ ለይቶ በዕርዕነው የሚል ታሪክም አለ ነገር ግን ቋንቋው የተያያዘ አንድ መሆኑን ሊቃውንት ይናገ

ወደ ገጽ ፲ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ርዕሰ አንቀጽ

## በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል

ጣራ ያለ ግድግድ ፤ ግድግዳ ያለ መሠረት ሊጸና አይችልም ። ለግድግዳውም ሆነ ለጣራው ዋናው መሠረቱ ነው ።

መሠረቱ በሚገባ የተመሠረተ ቤት ለባለቤቱ ከፍ ያለ ጥቅምን የሚያበረክት ሲሆን መሠረቱ ያልጸና ቤት ግን ኃይለኛ ነፋስ በነፈሰና ጐርፍ ባጐረፈ ጊዜ ፈራርሶ ይወድቃል ቤቱም ሲፈራርስ በውስጡ ተጠልለው የሚኖሩት ሰዎች መጠጊያ በማጣት እጅግ በጣም ሊሠቃዩ ይችላሉ ።

እንደዚህ ያለ ከባድ አደጋ እንዳይደርስ በማሰብ ቤት የሚሠሩ ሰዎች ሁሉ ከጣራውና ከግድግዳው በይበልጥ የሚጠነቁት ከመሠረቱ ላይ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ሲያስተምርበት በነበረው ወቅት ቃሉን ሰምቶ በሥራ የሚተረጉመውን ሰው ቤቱን በአለት ላይ መሥርቶ በሠራ ጥበበኛ ሰው መስሎ ሲናገር ቃሉን ከሰማ በኋላ በሥራ የማያውለውን ሰው ደግሞ ቤቱን በድቡሽት ላይ በሠራ ሰነፍ ሰው መስሎታል ማቴ. ፯ ፳፬.፳፯ ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ እስከ ዛሬ ከእግዚአብሔር ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል ። ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ባለሀገሮችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል ፤ የማዕዘኑም ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ አብራችሁ ትሠራላችሁ ብሏል ። ኤፌሶን ፪.፲፫ - ፳ ።

በተጨማሪም ይኸው ሐዋርያ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "አስተናደፍኩ መሠረተ ከመ ጠቢብ ሊቀ ጸረብት ወመሠረቱሂ ኢየሱስ ክርስቶስ " እንደብልሃተኛ የአናጺዎች አለቃ መሠረትን መሠረትኩ መሠረቱም ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብሏል ። (1ኛ ቆሮ ፫. ፲ ።)

ለማንኛውም ፍጡር አስገኙና መሠረቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደመሆኑ መጠን ሁሉንም ፍጥረትእንደጠባቂናእንደፍላጐቱ ይጠብቀዋል።ይመግበዋል ። ያስተዳድረዋል ፤ እርሱን መሠረት አድርጎ ሥራውን የሚሠራ ሰው ሁሉ የጀመረውን ሥራ ሁሉ ከፍጻሜ ለማድረስ ይችላል ። በክርስቶስ ትምህርት የተመሠረተ ሕዝበ ክርስቲያን ክርስቶስ የሠራውን ሥራ ለመሥራት የሚያዳግተው ነገር አይኖርም ። ራሱ ክርስቶስም "እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ። ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል ብሏል ። የዮሐ. ወን. ፲፬. ፲፪ ።

ነብያትና ሐዋርያት ስለክርስቶስ በሥጋ መገለጥ ሲያስተምሩ እንዳያስተምሩ ቢከለከሉም ስለእግዚአብሔር ያላቸውን መንፈሳዊ ፍቅር ሳያቋርጡ ስለአስተማሩ ማስተማራቸው እንደወንጀል ተቆጥሮባቸው እጃቸውንና እግራቸውን በገመድ እየታሠሩ አንዳንዶቹ ወደነበልባለ እሳት ሲወረወሩ አንዳንዶቹ ደግሞ ለተራቡ አራዊት ምግብ ሆነው ቀርበው ነበር ።

ነገር ግን የእሳቱ ነበልባል እንደበረዶ ቀዝቅዞላቸዋል ። አራዊትም ገርመውላቸዋል ። ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲገልጽ "እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ ጽድቅን አደረጉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አገኙ የአንበሶችን አፍ ዘጉ የእሳትን ወላፈን አጠፉ ከሰይፍ ስለት አመለጡ ከድካማቸው በረቱ በጦርነት ኃይለኞችሆኑ የባዕድን ጭፍሮች አባረሩ ብሏል ። ዕብ ፲፩.፴፫ ። እንግዲህ ሁላችንም በክርስቶስ ስም አምነን የተጠመቅን በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የታነጽን ስለሆነ እነርሱ የሠሩትን ሥራ ለመሥራት መዘጋጀት ይኖርብናል ።

የነቢያትንና የሐዋርያትን ታሪክ የምንመለከተው በከንቱ ሳይሆን እነርሱ የሠሩትን መልካም ሥራ ለመሥራት የምንችልበትን ቀና መንገድ ለመቀየስ እንድንችል ነው ።

አባቶቻችን ሐዋርያት ለስብከተ መንጌል ሲሠማሩ ብዙ ችግር ደርሶባቸዋል ። ነገር ግን የሚደርስባቸውን ችግር ቀደም አድርገው ተረድተውት ስለነበር ከመንፈሳዊ ዓላማቸው ወደኋላ አላሉም ። ሁሉንም በእግዚአብሔር ኃይል ድል እያደረጉ የወንጌልን ቃል ለመላው ዓለም ለማዳረስ ችለዋል ።



ለሐዋርያት የተሰጠው ኃይለ እግዚአብሔር አሁንም ቢሆን ለእግዚአብሔር አማኞች ሁሉ ይሰጣል የእግዚአብሔር ስጦታ በጊዜ ሊወሰን አይችልም ልቡናቸውን ከቂም በቀል ከኃጢአት ወዘተ ላነጹ ምእመናን እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ አይታገድም ይሰጣል ።

ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚያምን በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት የፀና ክርስቲያን ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ጸጋ እንደግል ስጦታ አድርጎ ሸሽጎ ማስቀመጥ አይገባውም ፤ ለምሳሌ በተራራ ላይ የተቆረቆረች ከተማ ከተመልካች ዓይን ለመሠወር እንደማትችል ሁሉ በክርስቶስ ስም ያመነ ክርስቲያንም ስለ ክርስቶስ አዳኝነት መመስከር አለበት እንጂ እምነቱን ሰውሮ መቀመጥ አይገባውም ።

ክቡር ዳዊት እንኳን በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረ ሰው ግዑዛን ፍጥረታትም ቢሆኑ ስለ እግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የሚመሰክሩ መሆናቸውን ሲገልጥ "ሰማዮች የአምላክን ምስጋና ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጆቹን ሥራ ያወራሉ ብሏል መዝሙር ፲፱. ፲፩ ። ይህ ሁሉ የሚያስረዳው ስለእግዚአብሔር አዳኝነት መመስከር የሚያስፈልገው ማንኛውም ፍጡር መሆኑን ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በርከት ያሉ አማኞች አሏት አብያተ ክርስቲያናትና ካህናቱም በቁጥር በርከት ያሉ ናቸው ። ካህናቱ ለሕዝበ ክርስቲያኑ የሚያቀርቡት መንፈሳዊ አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን የሚሠለጥኑባቸው ት/ቤቶች ተከፍተዋል ። ቅዱስ ሲኖዶስ በተከፈቱት የካህናት መሠልጠኛች ሳይወሰን ሌሎችንም ማሠልጠኛዎች ከፍቶ ካህናትን በብዛት ለማሠልጠን ሰፋ ያለ ዕቅድ ያለው መሆኑ ታውቋል ።

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያም ካህናት በትምህርተ ወንጌል እየሠለጠኑ ሌላውን ሕዝበ ክርስቲያን እንዲያስተምሩ ለማድረግ በርከት ያሉ ሰባክያንን በየቦታው እየላከ ያስተምራል ። የሚሰጠውም ትምህርተ ወንጌል በአየር ላይ ተበትኖ እንዳይቀር መጽሔቶችንና ጋዜጦችን እያዘጋጀ ለምእመናን ያቀርባል ።

ለዚህ ሁሉ መሠረቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ከላይ ተገልጿል ። ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል "፬. ፴፪ - ፴፰" የሚዘራና የሚያጭድ አብረው ደስ ይላቸዋል ። የዘለዓለም ሕይወት ፍሬንም ይሰበስባሉ ፤ አንዱ ይዘራል ፤ አንዱም ያጭዳል የሚለው በዚህ እውነት ሆኖአልና እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ላክኋችሁ ሌሎች ደክሙ እናንተ በድካማችሁ ገባችሁ" ብሏል በሚዘራ የተመሰሉ ነቢያት ሲሆኑ በአጫጅ የተመሰሉ ደግሞ ሐዋርያት ናቸው ። ነቢያት ክርስቶስ ይወርዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት ቢናገሩ ሐዋርያት ከዘመኑ ደርሰው ወረደ ተወለደ ብለው ቢያስተምሩም መሠረት አድርገው የተነሡት ክርስቶስን በመሆናቸው የወጡት ዓላማ ሁሉ ተከናውኖላቸዋል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው በነቢያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ የታነጽን በክርስቶስ ስም ያመን ሁላችን ስለ ክርስቶስ አዳኝነት የማስተማርና የመመስከር ግዴታ አለብን ።



www.ethiopianorthodox.org

# እናታችን ጽዮን

ከሁሉ አሥቀድሞ ታላቅ ኃይል ይገኝበታል ተብሎ ተስፋ ወደተጣለባት ጽዮን እየተባለች ወደምትጠራው ስም ያተኮርን እንደሆነ ጽዮን የእምባ የተራራ መጠሪያ ሆኖ እናገኘታለን ። ምክንያቱም ዳዊት በዚያ ዘመን ጽዮን እየተባለች በምትጠራው ተራራ መሽጎና ተከታዮችንም በዙሪያዋ አሰልፎ ረዘም ላለ ጊዜ ከጠላቶቹ ጋር ሲዋጋበት ቆይቶአል ታላቅኃይልም አግኝቶ ድልን ከተጐናፀፈ በኋላ የእስራኤልን የመንግሥት አስተዳደር በሚያቋቁምበት ወቅት ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ከመዛወሩ በፊት ከተማውን ከትሞ የህሌና እረፍት የልብ ሰላም አግኝቶ በደብረጽዮን ተቀምጦ እንደነበር ታሪክ የመዘገበውን እናነባለን ።

በተጨማሪም ጽዮን ኢየሩሳሌም የእግዚአብሔር ከተማ የእግዚአብሔርም መኖሪያ መሆኑዋን ይነግረናል ። ይህንንም የሚያረጋግጠው ዳዊት በመዝሙር ፸፮ በቁጥር ፪ "ሥፍራው በሳሌም ማደሪያውም በጽዮን" ነው ። ሲል ዘምሮ እናገኘዋለን ። በመዝሙር ፻፴፬ በቁጥር ፳፩ ደግሞ "በኢየሩሳሌም የሚያድር እግዚአብሔር ከጽዮን የተባረከ ነው። ብሎአል ይህ አባባል የከተማይቱን መጠሪያ የሚያመለክት ሲሆን ጽዮን የሚለው ስም ግን ከተማይቱን ብቻ ሳይሆን በከተማይቱ ውስጥ የሚኖረውን ሕዝብ ጭምር መጠሪያ ሆኖ አገልግሎአል ። ይኸውም ከጊዜ ብዛት የተነሳ በብሉይ ኪዳን የነበረው የምእመናን ማኅበር ሁሉ የሚጠራበት ስም ሆኖ ኑሮአል ።

ይህንንም ለመረዳት ብንሻ በመዝሙር ፻፵፱ በቁጥር ፲፪ "ምስጋናው በቅዱሳን ጉባኤ ነው ። እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው ። የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሃሤትን ያድርጉ ።" ብሎአል እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው የዳዊት መዝሙሮች እግዚአብሔር ጌታዋና ማደርያው የሱ መኖሪያው በመሆኑዋ ጽዮን ምን ያህል የታደለች ከተማ እንደሆነች የሚናገሩ ናቸው ። እግዚአብሔር መኖሪያው በጽዮን ስለሆነ በዚያ ያለው ሕዝብ ምን ጊዜም ቢሆን አይናወጥም ረድኤቱ እርሱ ነው ።

ጽዮን ተራራ እና የከተማ መጠሪያ ስም መሆኑዋን ባጭሩ ካየን እናታችን ጽዮን የተባለችበትን ሁኔታ ደግሞ እናብራራለን የቃል ኪዳኑ ታቦት የሆነችው ጽዮን የእግዚአብሔር ቃሉና ስሙ የተጻፈበት እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ጽላት ናት አሪት ዘዳግም ፲.፲ ይህችም የሙሴ ጽላት በየአመቱ ኅዳር ፳፩ ቀን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስካሁን ድረስ የምትከበርበት የሠራቻቸውን ታላላቅ ኃይሎች በማስታወስ ነው ።

ይኸውም "ኤሎፍላውያንና የእስራኤል ሕዝቦች ታላቅ ውጊያ አደረጉ ። በውጊያውም እስራኤውያን ድል ሆኑ የሙሴ ጽላትም በኤሎፍላውያን ተማረከች የአዛጦን ሰዎችም የሙሴ ፅላትና የነሱ ጣኦት ዳጎን ወደ አለበት ሥፍራ ማልደው ገቡ ። ቤታቦተ ጽዮን ኃይል የተቀጠቀጠው ዳጎን በእግዙአብሔር ታቦት ፊት በግንባሩ ወድቆ ነበር ። የጣዖቱ የዳጎን ራስና እጆቹ ተቆርጠው በመድረኩ ላይ ወድቀው ነበር ። ከዚህም ፍርሃት የተነሳ የዳጎን ካህናት ወደ ዳጎን ቤት የሚገቡት ሁሉ በአዛጦን ያለውን የዳጎንን መድረክ እስከ ዛሬ ድረስ አይረግጡም ይባላል ።

ሌላው ደግሞ የእግዚአብሔር እጅ በታቦተ ጽዮን አድሮ በአዛጦን ሰዎች ላይ ከበደባቸው ። አጠፋቸውም እስከ ድንበራቸው ድረስ በእባጭ መታቸው እነርሱም ይህንን መቅሰፍት ባዩ ጊዜ በእኛና በአምላካችን በዳጎን ላይ እጁ ጠንክራለችና የእስራኤል አምላክ ታቦት ከእኛ ዘንድ አይቀመጥ አሉ ።

ነገሩ በዚህ ብቻ አልቆመም የእግዚአብሔር ታቦት በሕዝቡ መጥፎ አድራጐት ስለተቆጣ እንደገና የእግዚአብሔር እጅ በታላቅ ድንጋጤ ከትንሹ እስከ ትልቁ ድረስ የከተማይቱን ሰዎች በእባጭ መታቸው ። የእግዚአብሔር ታቦት ወደአስቀሎና እንዲሄድ አደረጉ" ፩ኛ/ ሳሙኤል ምዕራፍ ፭ ከቁጥር ፩-፲፪ ኃጢአተኛና በደለኛ ሆነው ወደ እግዚአብሔር በንስሐ ያልተመለሱትን ሰዎች የእግዚአብሔር ታቦት የሆነችው ጽዮን በመቅስፈትና በእባጭ እንደቀጣቻቸው ተገንዝበናል ።

"አቢዳራ ግን ታቦተ ጽዮንን ተቀብሎ መኖረያ ቤቱን ለቆ በውስጡ እንድትኖር አደረገ ። እርሱም እያከበረ ሌላው እንዲያከብር አደረገ ። ይህንን በማድረጉ በታቦተ ጽዮን አድሮ የሚኖረው እግዚአብሔር ቤቱን በበረከት ሞላለት በየጊዜው የተደረገውን መቅሰፍት ፈርቶ የነበረው ዳዊትም የአቢደራ ቤት በበረከት መሙላቱን በሰማ ጊዜ የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ከተማው እንድትመጣለት ፈለገ ታቦተ ጽዮንም ወደ እርሱ በመጣች ጊዜ እየዘመረ ተቀበላት ድንኳንም ተክሎ የእግዚአብሔርን ታቦት በድንኳን ውስጥ አስገባት ታላቅ በዓልም አደረገ ። የሚቃጠልና የደህንነትም መስዋዕት አቀረበ ሕዝቡንም በእግዚአብሔር ስም መረቀ ለሕዝቡም ሁሉ ለየአንዳንዱ ወንድና ሴት አንዳንድ እንጀራ ፣ አንዳንድ የሥጋ ቁራጭ አንዳንድ የዘቢብ ጥፍጥፍ አከፋፈለ ።

፪ኛ/ ሳሙኤል ምዕራፍ ፮ ቁጥር ፲. ፲፱ ዳዊት ይህን መልካም አድራጐት የፈጸመው የእግዚአብሔር ታቦት በሆነችው የጽዮን በዓል በሚከበርበት ዕለት ነበር ። ዛሬም ቢሆን ማንኛውም ክርስቲያን የጽዮንን በዓል ለማክበር በየአመቱ ለሚመጡት እማኞች ሁሉ ዝክር ማኅበር ፣ ደግሶ ቢጋብዛቸው ቤት ንብረት ለፈረሰባቸው ሰዎች ካለው ቢያካፍላቸው ዳዊት ያገኘውን በረከት እንደሚያገኝ የታመነ ነው ።

[illegible] ደግሞ ዳዊት ረዘም ላለ ጊዜ በድንኳን አስቀምጧት የነበረችውን ታቦት ጽዩንን ሰለሞን ቤተ መቅደስ



ሰርቶ በውስጡ እንድትኖር አደረገ ፩ኛ/ ነገሥት ምዕራፍ ፰ ከቁጥር ፩-፲ ይህንንም በማድረጉ እግዚአብሔር በታቦተ ጽዮን አድሮ ታላቅ በረከት ሰጠው ግዛቱንም የሰላም ዘመን አደረገለት እግዚአብሔርም ጦርን ቀስትን እነዚህን የመሣሠሉትን የጦር መሣሪያዎች ሁሉ ሥላጠፋለት በዘመኑ ጦርነትና የረሃብ ሥቃይ አልነበረም ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ታቦት እያከበረና ቅንን ፍርድ እየፈረደ በእግዚአብሔር ሕግ ይመራ ስለነበር ነው ።

እንግዲህ ጽዮን እናታችን መሆኑዋን በአርዕስቱ እንደጠቀስን ይታወሳል ። ዳዊትም በመዝሙር ፹፮ ሰው ሁሉ እናታችን ጽዮን ይላል። "ሲል ዘምሮአል ለጊዜው ታቦተ ጽዮንን ሲሆን ፍፃሜው ግን ቅድስት ድንግል ማርያምን ነው ። ይኸውም ድንግል ማርያም ለዓለም ሁሉ መንፈሳዊት እናት መሆኑዋን ያረጋግጣል ። ስለ እርሷ በንትቢት የተነገረው ሁሉ በተግባር ተፈፅሞአልና ከላይ በተጠቀሰው በመዝሙር ፹፭ ቁጥር ፫-፮ እንደተገለጠው ሁሉ" ረዓብ ማለት የግብፅ አገር ሰው ባቢሎናውያን የጢሮስም ሕዝቦች ኢትዮጵያውያንም በጽዮን የተወለዱ ናቸው ተብሎ ትንቢት ተነግሮ ነበር ። ይህም ማለት ከድንግል ማርያም በተወለደው በክርስቶስ አምነው ከኃጢአታቸው ይድናሉ ። የክርስቶስ የመንፈስ ልጆች ይሆናሉ ። ቅድስት ድንግል ማርያምም ለነዚህ ሁሉ የመንፈስ እናታቸው ትሆናለች ማለት ነው ። ይኸውም በመንፈሳዊ አኳኋን አሕዝብ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ይቆጠራሉ እግዚአብሔርም ሕዝቦችን በሚቆጥርበት ጊዜ በእርሱ የሕይወት ጽሑፍ የተጻፉትን ለይቶ ሲመለከታቸው በጽዮን አገር የኖሩትን መንፈሳዊያን ዜግነታቸውን እንዳወቀላቸው ሁሉ በቅድስት ድንግል ማርያም የሚያምኑትን ምዕመናን ሁሉ ጸሎታቸውንና ልመናቸውን ሁሉ ይሰማቸዋል ።በሕይወት መጽሐፍም ይጽፋቸዋል ።

ስለዚህ እኛም መልካም ሥራ ሠርተን በሕይወት መጽሐፍ እንድንጻፍና መንፈሳዊ ዜግነታችን ታውቆ የክብሩ ወራሾች እንድንሆን ለአገልግሎት እንሰማራ ቅድስት ድንግል ማርያምም መንፈሳዊት እናታችን ስለሆነች እናታችን ጽዮን እያልን ሁል ጊዜ እንዘምርላት ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



www.ethiopianorthodox.org

# ወደ ሀገርህ ተመለስ

አንድ ሰው ተወልዶ ያደገበትን ቦታ ትቶ ወደሌላ አገር ሲሔድ ያ ተወልዶ ያደገበት ዕትብቱ የተቀበረበት ሲንቧችና ሲድሕ የነበረበት ሜዳ ኩብት በግ ፍየል ሲአግድ የነበረበት ተራራው ወንዙ ሸለቆው ሸንተረሩ ትዝ ይለዋል ሁል ጊዜ በሕሊናው ሲወጣና ሲወርድ የሚኖረው በሕፃንነቱ ሲያደርገውና ሲሰራው የነበረው ትዝታ በአእምሮው ተቀርፆ ይኖራል ትውስ ሲለው ሲናፍቀው የተወለደበትን አገር ተመልሶ ለማየት ሲችል ደስታው እጥፍ ድርብ ይሆናል ፡፡

በዚህ ጽሑፋችን ልንገልጸው የፈለግነው መድኃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በሕፃንነቱ ወራት ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር የተወለደበትን አገር ናዝሬትን ትቶ ስለሔደና ስለደረሰበት ስደት ነው ፡፡ ሁሉንም ማድረግ የሚቻለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሕፃናት ተወልዶ ቀስ በቀስ አደገ እንደ ሰውም መከራን ከልጅነቱ ጀምሮ ተቀበለ እንጅ እንደ አምላክነቱ ሁሉን ነገር አንድ ጊዜ ልፈጽመው አላለም በዚሕም መሰረት በአውግሥጦስ ቄሣር ዘመነ መንግሥት ሲወለድ ሄሮድስ ኢየሩሳሌምን ይገዛ ነበር በዚያን ጊዜ የጌታችን የኢየሱስን መወለድ ይጠባበቁ የነበሩ የምሥራቅ ሰዎች ሰብአ ሰገል ወርቅ ዕጣን ከርቤ ይዘው ለተወለደው ሕፃን ሊሰግዱ በኮከብ እየተመሩ መጡ፡፡

ነገር ግን ይመራቸው የነበረው ኮከብ ቤተ ልሔም ሲደርስ ለጊዜው ስለተሠወራቸው ወደ አገረ ገዥው ወደ ንጉሡ ሄሮርድስ ዘንድ ቀርበው የአይሁድ ንጉሥ የተወለደው የት ነው? ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናል አሉት ሄሮድስም ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ነገሩን የሚያውቀው ስለነበርና ከሱም ሌላ የአድሁድ ንጉሥ እንደሌለ አስቦ ደነገጠ በዘመኑ ያሉትን ካህናትንም ስለዚህ ነገር በስውር አስጠርቶ አነጋገራቸው /ጠየቃቸው/እነሱም አዎ አንች ቤተ ልሔም የይሁዳ ምድር ከይሁድ ገዥዎች ሁሉ ከቶ አታንስም ከዳዊት ዘር የሆነ ሕዝቤን እስራኤልን የሚጠብቅ መስፍን ከአንች ይወለዳልና ተብሎ ተጽፎ አል አሉት ፡፡ ንጉሡ ሄሮድስም ይህንን ከካህናቱ ከተረዳ በኋላ ሰብአ ሰገልን አስጠርቶ ሁኔታውን ነገራቸው ሲአገኙት ለእሱ እንዲነግሩት እሱም እንደሚሰግድለት ነግሮ ላዩ አልጋ ውስጡ ቀጋ ሐሳቡን ነገራቸው እነሱም ሕፃኑን አግኝተው ሰገዱለትና ስጦታቸውን ከአቀረቡለት በኋላ በመጡበት መንገድ ሣይመለሱ በሌላ መንገድ ወደሐገራቸው ገቡ ፡፡ ሄሮድስም እነሱ መጥተው ይነግሩኛል በማለት ሲጠባበቅ ሰዎቹ ሣይመለሱ ቀሩ ከዚህ የተነሣ ነው ንጉሡ በቁጣ መንፈስ ተነስቶ የነገሩትን ዘመን ከቆጠረ በኋላ ዕድሜአቸው ሁለት ዓመት የሆኑትን ሕፃናት ሕፃኑን ክርስቶስን አገኘሁ በሚል ተስፋ አንድ መቶ አራት ሺህ /አሥራ አራት ዕልፍ ከአራት ሺህ ሕፃናትን አሳረደ፡፡

ነገር ግን ከዚህ ቀደም ሲል መልአኩ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጾ ሕፃኑን ሄሮድስ ሊገድለው ይፈልገዋልና ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ወደ ግብፅ ይዘኸው ሽሽ በማለት ነግሮት ስለነበር ዮሴፍም ከመልአኩ በተነገረው መሰረት ሕፃኑን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ይዞ "ልጄን ከግብፅ ጠራሁት" ተብሎ በነቢዩ ሆሴዕ ፲፩-፪ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ወደ ምድረ ግብፅ ወረደ ፡፡

በዚያም በግብፅ ምድር በመከራ በረሐብ በሥቃይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ተቀመጡ እነሱም በዚያ ሣሉ ያ ሕፃኑን ይፈልገውና ለመግደል ያሳድደው የነበረው ንጉሥ ሕፃኑን ሊገድልና ዕፎይታ ሲአገኝ ቀርቶ ሐሳቡ ሣይፈፀምለት እነዚያን ሁሉ ሕፃናት በግፍ ከጨፈጨፈ በኋላ የሰው ዕድሜ ተራ ሰው ቢሆን ዕድሜው ውሱን ነውና እገሌ ሀብታም ወይም እገሌ ትልቅ ሰው ነው ይቆይ እገሌ ተራ ሰው ነው ወይም ደሐ ነው ይሙት ብሎ የማይመርጠው ሞት ጠራውና የግዛቱን ዘመን ለማራዘም በማሰብ ይህን ያህል ሕፃናትን የፈጀው ሄሮድስ ሞተ ፡፡

በዚህ ጊዜ ነው መጀመሪያ ሕፃኑን ሄሮድስ ሊገድለው ይፈልገዋልና ወደ ግብፅ ይዘኸው ሽሽ ብሎት የነበረው መልአክ አሁንም እንደገና በራዕይ ለዮሴፍ ተገልፆ የሕፃኑን ነፍስ ይፈልጉት የነበሩት ሞተዋልና ተነሳ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሒድ ያለው ዮሴፍም እንደተነገረው ሕፃኑን እናቱንም ይዞ ወደ እስራኤል አገር ገባ እንዲገደል ውሣኔ አሣልፎ ሲሯሯጥ የነበረው ሞቶ ነገሩ የተዛወረ ሆነ ይህ ነው የሰዎች አቅም ፡፡ ሰዎች አቅማቸው የፈቀደላቸውን ሥራ መሥራት ትተው ከአቅምቸው በላይ የማይችሉትን ሥራ ለመሥራት ሲያንጋጥጡ ሥራቸው ውጤት አልባ ከመሆንም አልፎ የራሳቸውም የሕይወት ፍጻሜ ይሆናል መጥፎ ሥራ ራስን እንጅ ሌላውን አይጐዳም ስለት ድጉሱን ዳባራሱን ተብሎአልና ፡፡

ሄሮድስ ፈጣሪው የሰጠውን የግዛት ዘመኑን ጨርሶ ማለፍ ሲገባው አቅሙ በላይ በሆነ አስተሳሰብ ዘለዓለማዊ ሥልጣን ለመኖሩን ባለመረዳቱና ሐሳብ ውስጥ በመሆኑ ይህንን የመሰለ ችግር ሲፈጥርና ይህንን ያህል ሕፃናት በግፍ ጨፈጨፈ የሕፃናቱም ጭፍጨፋ በዚህ ዓለም ከተወሰነለት የግዛት ዘመን አንዷት ሰዓት እንኳን አልጨመረለትም እንዲያውም የአድረገው ግፍና ጭካኔ እስካሁን ድረስ እንዲህ ላሉ ግፈኞች ምሳሌ ሆኖ ቆይቶአል ወደፊትም ይኖራል ፡፡

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የዚህን የመድኃኒታችንን የሕፃኑን ክርስቶስንና የእመቤታችንን የቅድስት ድንግል ማርያምን የዮሴፍንና የሰሎሜን የስደት ጊዜ ዘመነ ጽጌ በማለት በየዓመቱ ከመስከረም ፳፮-ኅዳር ፮ ቀን ድረስ በፀሎት በማህሌት በቅዳሴ መታሰቢያነቱን ወስና ታከብረዋለች ፡፡

ፍሥሐ ባንቲ



# አቡነ ጰንጠሌዎን

አቡነ ጰንጠሌዎን የትውልድ አገራቸው ሮም ሲሆን አባታቸው በሮሙ ንጉሥ ባለመዋልነት ካላቸው ሮማውያን መኳንንት አንዱ ነው፡፡ወላጆቻቸው ካህንና የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ እንዲሆኑላቸው ብርቱ ምኞት ስለነበራቸው ልጃቸው አቡነ ጰንጠሌዎንን ከሕፃንነታቸው ጀምረው በመንፈሳዊ ትምህርት እንዲያድጉና በምሥጢረ መጻሕፍት እንዲራቀቁ ከመንፈሳዊ ትምህርት ቤት አስገቧቸው ፡፡

አቡነ ጰንጠሌዎን ከዚያው ከመንፈሳዊ ት/ቤት እንደ ገቡ የእግዚአብሔርን ቃል እየተከታተሉ ካደጉ በኋላ የዚህን ዓለም ክብርና ተድላ ደስታ ንቀውና መንነው ከእነ አቡነ አረጋዊ ጋር ወደ ግብጽ ሄደው በአባ ጳኩሚስ እጅ አልባሰ ምንኩስናቸውን ለበሱ ፡፡ ከዚህ ውጣ ውረድ የበዛበትም ዓለም ተለይተው በአንድ ዋሻ ተከተው እንዲኖሩ በብሕትውና መኖርን መረጡ ፡፡

አቡነ ጰንጠሌዎን ለተወሰነ ጊዜ በአባ ጳኩሜስ ገዳም ከቆዩ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ በራሳቸውም ሐሳብ ከገዳሙ ወጥተው ወደ ሮም ተመልሰው በሮም አካባቢ ይኖሩ የነበሩት ሕዝብ ጣዖትን እያመለኩ ኃጢአትንም እየሠሩ የሚኖሩ ሕዝብ ስለነበሩ እነሱን ለማስተማር በየክፍለሀገሩና በየአውራጃው እየተዘዋወሩ የወንጌልን ትምህርት በሰፊው አካሂደዋል ፡፡ ብዙ ሕዝብንም በትምህርተ ወንጌል ከኃጢአት ወደ ጽድቅ መልሰዋል ፡፡

አቡነ ጰንጠልዎን ይህ የማስተማር ተግባር በሮም ብቻ ሳይወሰኑ እንደገና ከሮም ተነሥተው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የወንጌልን ትምህርት ለማዳረስና ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትን ለማስፋፋት ጥረት ካደረጉና ተሳንቱ ቅዱሳን በመባል ከታወቁት አንዱ ናቸው ፡፡ ፱ቱ ቅዱሳን በትግራይ ክፍለ ሀገር በተለይ በአክሱምና በአድዋ አውራጃዎች ሁሉም ተባብረው ወንጌልን አስተምረው ካበቁ በኋላ ወደ የበዓታቸው በሚለያዩበት ወቅት አቡነ ጰንጠሌዎን ከአክሱም ከተማ በስተምሥራቅ ወደምትገኘውና ፪ ኪሎ ሜትር ያህል ርቀት ካላት ተራራ ላይ ወጥተው ተቀመጡ ከዚያች ተራራ እንደገቡ ከተራራው ውስጥ ትንሽ ዋሻ ስላገኙ ከዚያች ውስጥ ፵፭ ዓመት ያህል ቆመው በጾምና በጸሎትም ተወስነው በልዩ ልዩ ትሩፋት ፈጣሪያቸውን ከማገልገላቸውም በላይ ያልተማረውን ሕዝብ እያስተማሩ በሽተኞችን እየፈወሱ ታላላቅ መንፈሳውያንና ብዙ ተአምራት እያደረጉ ኖረውአል ፡፡ ገድላቸው እንደሚነግረን ጻድቁ አቡነ ጰንጠሌዎን የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃል ነው እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም የሚለውን አምላካዊ ቃል በማስታወስ ከእህል ከውኃ ተከልክለው እንደመላእክት ምስጋናውን የእግዚአብሔርን ቃል ምግብ አድርገው ይኖሩ ነበር ፡፡

አቡነ ጰንጠሌዎን ይህን ያህል ተጋድሎ ሊያደርጉ የቻሉና ፵፭ ዓመት ቁመው የኖሩት በራሳቸው ኃጢአት ወይም በወላጆቻቸው በደል ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ በማሰብና ስለ ሰው ልጅ ሲል በመስቀል ተሰቅሎ ራሱን ለሞት አሳልፎ የሰጠበትን ቀን በማስታወስ ነው ፡፡

አቡነ ጰንጠሌዎን ፈጣሪያቸውን ለማገልገልና እሱን ደስ ለማሰኘት ያደረጉት ተጋድሎ ተጽፎም ባላለቀም ነበር ከዚህም ሌላ (ሕሱ ሰላማ ለብሔር) "ላላችኑባት ሀገር ሰላምን ፈልጉ ስለ እርስዋም ወደ እግዚአብሔር ጸልዩ ሲል ነቢዩ ኤርምያስ የተናገረውን ኤር ፳፱፡ ፯ በማስታወስ ስላሉባት ሀገር ስለ ኢትዮጵያም ወሰን የሌለውን ጸሎት ሲጸልዩ ኖረዋል ፡፡ኢትዮጵያ በሰላም እንድትኖር ከጠላትና በክፉ ዓይን ከሚመለከቷትም ሁሉ ነጻ ሁና እንድትኖር ም ነው ፵፭ ዘመን ደክመኝ ስለሯን ሳይሉ ቁመው የነበሩት ፡፡

የአቡነ ጰንጠሌዎን ትሩፋት በዚህ አላተወሰነም አንድ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቅ ፊንሐስ መምሕላይ የተባለ አይሁዳዊና ከሃዲ ተነሥቶ በናግራን የነበሩትን ክርስቲያኖች ይፈጃቸው ጀመር በዚህ ጊዜ አጼ ካሌብ በአድራጐቱ አዝኖ እነሱን ለመርዳት ስላሰበ በቀጥታ ወደ አቡነ ጰንጠሌዎን ዋሻ ሄዶ ነገራቸውና እነሱንም ለመርዳት ፍላጐት እንዳለው ገለጸላቸው ከዚህ በኋላ አቡነ ጰንጠሌዎን አጼ ካሌብን ከመባረካቸውም በላይ በል ሂድ እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን አሁንም ድል አድርገህ ተመለሳለህ ብለው መርቀው ሲያሰናብቷቸው መሬቱ ከእኩሉም ተከፍቶለት ውስጥ ለውስጥ ሄዶ በናግራን ወጣ በዚህ ጊዜ ክርስቲያኖችን ሲያሰቃያቸው የነበረውን ከሃዲ ከእነ ሠራዊቱ አጥፍቶና ደምስሶ በዚያው በመጣበት ጉድጓድ ውስጥ ለውስጥ ሲመለስ ሠራዊቶቹ ሲሄዱ ወርቁ ሽዋ ሽዋ ሲል ሰምተው ምን ይሆን በማለት ገሚሶቹ ፫ እፍኝ ገሚሶቹ ፪ እፍኝ ገሚሶቹ ደግሞ ጨርሰው ሳይዙ ወጡና ከብርሃን ደርሰው የያዙትን ቢመለከቱ የሁሉም ወርቅ ሆኖ አገኙት በዚህ ጊዜ ብዙ የያዘ ምነው በጨመርኩበት እለ ጥቂት የያዘም እንደዚሁ ምነው በጨመርኩበት ብሎ ሲያዝን ጨርሶ ያልያዘ ደግሞ ምነው እንደ እናንተ በያዝኩ ሲሉ ሰምቶ አጼ ካሌብ የዘነ (አዘነ ያልዘነም አዘነ አለ ይባላል ፡፡

አቡነ ጰንጠሌዎን የሕይወታቸውን ታሪክ ስንመለከት መላ ዘመናቸውን ያሳለፉት ወንጌል ያልደረሰበትን በማዳረስ ፡ ያልተማረውን በማስተማር የታመመውን በመፈወስ እንዲሁም የሰውን ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ ነበር ፡፡

ይህንን ሁሉ መንፈሳዊ ሥራና ተልእኮቸውን ፈጽመው "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ ሩጫየንም(በወንጌል ትምህርት) ፈጽሜአለሁ ወደፊት የ



www.ethiopianorthodox.org

ጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል” ፪ኛ ጢሞ. ፬ ፡ ፯ በማለት የሚቆያቸው ሰማያዊ ክብር እያስደሰታቸው ጥቅምት ፯ ቀን ከዚህ ምድራዊ ዓለም ወደ ሰማያዊ ዓለም ተሸጋግረዋል ከሚያልፈውና ከሚጠፋው ዓለም ወደ ማያልፈውና ወደማይጠፋው ዓለም ተጉዘዋል ።

ዛሬም ቢሆን እንደ አቡነ ጳንጠሌዎን የመሳሰሉት ደጋግ አባቶች እግዚአብሔርን በማገልገል ሰማያዊ ቤታቸውን አደራጅተው ከዚህ ዓለም ቢለዩ ቢሞቱ አይባልም ፤ ምክንያቱም ደጋግ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞት በሚለዩበት ወቅት ከክብር ወደ ክብር ከኀዘን ወደ ደስታ ስለሚሸጋገሩ ትንሽ ቅሬታ አይሰማቸውምና እንዲያውም (ዝክረ ጻድቅ ለዓለም ይሄሉ) “የጻድቅ መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ በበጎ አጠራር ሲጠሩና በመልካም ስም ሲወሳ ስለሚኖር ነው ።

ስለዚህ ሰው ሁሉ እግዚአብሔርን በማገልገል ከፈጣሪው የሥራውን ዋጋ የሚያገኝበትንና እነ አቡነ ጳንጠሌዎን ወደገቡበት ቦታ ለመግባት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው ።

ራስን በሥራ ማነጽ እንጂ የሌላውን ክብር ሲያወሩ መኖርና በሌላ ሰው ሥራ ሲደነቁ መታየት ዋጋ አይኖረውም ። ስሁሉም የሰው ልጅ በጻድቃን መንገድ እንዲራመድ የእግዚአብሔርን ስም ከማስታወስ መቆጠብ የለበትም የእግዚአብሔርንም ስም የጠራ ሁሉ ይድናል ተብሎ ተጽፏልና ።

ክነፈ ርግብ ማርቆስ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከምታከናውናቸው መንፈሳዊያን ሥራዎች አንዱ ካህናትን እያሠለጠኑ እንዲያስተምሩ ማድረግ ነው።

የተማሩትን ካህናት በአጭርና በረዥም ጊዜ እያሠለጠኑ እንዲያስተምሩ ለማድረግ የሚያስችሉ ስድስት ማሠልጠኛዎች ተከፍተው ሥራቸውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ ። የካህናቱ ማሠልጠኛዎች ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችላቸውን ገንዘብ የሚያገኙት ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ።

ከውጭ ሀገር አብያተ ክርስቲያናት የሚላከውን የእርዳታ ገንዘብ እየተቀበለ ለካህናት ማሠልጠኞች ት/ቤቶች የሚያከፋፍለው የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ፡ ማሠልጠኞች የአከናወኑትንና የሚያከናውኑትን ተግባር ለመገምገም ይችል ዘንድ ከጳጉሜን ፫ቀን እስከ መስከረም ፲ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ድረስ ለመጀመሪያ ጊዜ የካህናት ማሠልጠኞች ሴሚናር (ዓውደ ጥናት) አድርጓል ስለዚሁ ሴሚናር እንዲያብራሩልን መጋቤ ምሥጢር ወ/ ሩፋኤል ፈተሒን ጠይቀናቸው የሚቀጥለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል ።

ሴሚናሩ ለቤተ ክርስቲያናችን የሥራ እንቅስቃሴ እጅግ በጣም የሚጠቅም መሆኑ የሚያጠራጥር ነገር አይደለም በዚሁ ሴሚናር /ዓውደ ጥናት/ ላይ ከተባበሩት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የእርዳታ ኮሚሽን አማካሪ ዶ ኢቲና ሞን ፍሬድ ሲገኙ በአምስቱም ካህናት ማሠልጠኛዎች የሚገኙ ብጹአን ሊቃነ ጳጳሳት አንድ ርዕሰ መምህራንና ሁለት መምህራንን በመጨመር ፬ት ፬ት እየሆኑ ተገኝተዋል በተጨማሪም ከጠቅላይ ቤተ ክህነት መምሪያዎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሲሳተፉ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የሥራ ሐላፊዎችም በሴሚናሩ ላይ ተሳትፈዋል ብለዋል ።

የሴሚናሩ ተሳታፊዎች ስለተወያዩባቸውም ሲያብራሩ በሴሚናሩ ላይ ብዙ ነገሮች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ቢያስፈልግ

፩ኛ/ ትምህርተ ሃይማኖት ፪ኛ/ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ፫ኛ/ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፬ኛ/ ልማት በቤተ ክርስቲያን ፭ኛ/ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ፮ኛ/ ስለ ሰበካ ጉባኤ ወዘተ ተወያይቷል ብለዋል ።

በአምስቱም የካህናት ማሠልጠኛዎች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች የተለያዩ ናቸው ይባላል ስለዚህ ሴሚናሩ የወሰደው እርምጃ አለን ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ

ጉዳዩ ተገልጾ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጎበት ሲያበቃ በሁሉም ማሰልጠኛዎች የሚሰጡት የትምህርት ዓይነቶች በአንድ ላይ እንዲዘጋጁ ጉባኤው ተወያይቶ ውሳኔ አስተላልፎአል በማለት ተናግረዋል ።

በአንዳንዱ ማሠልጠኛዎች የመምህራን እጥረት ስላለ ያልሠለጠኑት መምህራን እንዲያስለጥኑ ይመደባሉ ስለሚባለው በተጨማሪ ሲያብራሩ በዕርግጥ ጉዳዩ አሳሳቢ በመሆኑ ውይይት ተደርጐበታል በመጨረሻም የዜማ የቅኔ የአቋቋም የመጻሕፍት ትርጉሜ መምህራንም ቢሆኑ ለማስተማር ከመመደባቸው በፊት እንዲሠለጥኑ ተደርጓል ከዚህም ሌላ እንዲህ ያለው ሴሚናር ዓውደ ጥናት ለሚሰለጥኑትም ሆነ ለሚያሠለጥኑት እጅግ በጣም ጠቃሚ ስለሆነ በየዓመቱ ሳያቋርጥ እንዲቀጥል ጉባኤው ተስማምቷል በማለት መጋቢ ምሥጢር ወ/ሩፋኤል ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

የካህናትን አገልግሎት በሕብረተሰቡ ዘንድ የተሟላ ለማድረግ እንዲቻል በየሀገረ ስብከቱ አልፈው አልፈው የተቋቋሙት የካህናት ማሠልጠኛዎች ለቤተ ክርስቲያናችን አለኝታዎች ናቸው ለማኑ የማድረግ ሐላፊነት ያለበት ይመስለናል ።

ከኢትዮጵያ አህጉር ስብከቶች በርከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና ካህናት ባሉባቸው የካህናት መሠልጠኞዎችም በለጠ ዘዴ ነው ።

ይህንንም ለማድረግ ሐላፊነት ያለው ቅዱስ ሲኖዶስ ስለሆነ ጉዳዩን አጥንቶ በሥራ ላይ እንደሚያውለው ተስፋ እና ደርጋለን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያ



ከተባበሩት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የርዳታ ኮሚሽን አማካሪ ንግግር ሲያደርጉ

ለት ያስደፍራል ።

ቅዱስ ሲኖዶስም በእነዚህ አሁን በተከፈቱት የካህናት ማሠልጠኛዎች ብቻ ሳይወሰን ሌሎችንም ማሠልጠኛዎች በመክፈት ካህናት በብዛት እንዲሠለጥ ለእያንዳንዳቸው ሊቋቋምላቸው የሚገገባ ነው እንላለን ከ፰ሺህ ያላነሱ ካህናት የሚገኙባቸውን አህጉረ ስብከቶች በሕብረት ማሠልጠኛ ከመክፈት ይልቅ ራሳቸውን አስችሎ ማሠልጠኑ ከሁሉ የ ናዊ ተራድኦ መምሪያም ከቅዱስ ሲኖዶስ ጋር በመተባበር ስለካህናት ማሠልጠኛዎች በብዛት መቋቋም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥባቸው ከሚገቡት ጉዳዮች አንደኛው መሆኑን እናሳስባለን ።

ቄ. ልሣነወርቅ በዛብህ





www.ethiopianorthodox.org

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ራሉ ስለዚህ አያከራክርም ። ጌታ ባረገ ጊዜ በ፴፫ኛው ዓመት ኔሮን ቄሣር በነ ገሠ በሰባት ተጀምሮ በስምንተኛው ተፈጽሟል ።

፮ኛ/ የተጻፈበት ለምን ምክንያት ለ ምን ነበር ለሚለው ፤

ሀ. ጌታ ከሕዝብና ከአህዛብ እንደተ ወለደ ለማስረዳት ማቴ ፩ ቁ ፳

ለ. ከድንግል ማርያም በግብረ መን ፈስ ቅዱስ በሁቱም ድንግልና እን ደተወለደ ለማስረዳት ማቴ ፩ ቁ ፲፰ ።

ሐ. ክርስቶስ ከዮሐንስ የሚበልጥ የ ዮሐንስ ፈጣሪ መሆኑን ለማስረ ዳት ማቴ ፫ ቁ ፲፩

መ. የነቢያት ጌታ የነቢያት ፈጣሪ እንደሆነ ለማስረዳት

ሠ. ኢጋንንትን በአሊቃቸው በብኤልዜ ቡል ሳይሆን በመንፈስእግዚአብሔር የሚያወጣቸው መሆኑን ለማስረ ዳት ማቴ ፲፪ ቁ ፲፰ ።

በተለይ ዮሐንስ የአንድነትን የሦስ ትነትን ምስጢር ጠለቅ አድርጐ ለማስ ረዳት ዮሐ. ፩ ቁ ፩ ም ፲፬ ቁ ፲፩ ም ፲፯ ቁ ፳፩ ። ያላመኑትን ለማሳመን አሪት በሙሴ አማካይነት ሲጻፍ ወንጌል ግን በሥጋ ተገልፆ ጌታ የሚያስተምረው ን እየተከታተሉ ነው የጻፉት ወይስ ተገ ልፆላቸው ለሚለው ።

ወንጌላውያን መንፈስ ቅዱስን ከተ ቀበሉ በኋላ ጌታ የአስተማረውን ቃል መንፈስ ቅዱስ እየመራቸውና እያተጋ ቸው ጽፈውታል መንፈስ ቅዱስ እያተ ጋቸውና እያስታወሳቸውም ቃሉን እን ደሚጽፉት እራሱ መድኃኒታችን ከእናንተ ጋር ሳለሁ ይህን ነገርኋችሁ ነገር ግን አብ በስሜ የሚልከላችሁ የእ ውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔ የነገርኋችሁ ንም ሁሉ ያሳስባችኋል ብሎአል ዮሐ ፲፬ ቁ ፳፭ ።

# የነቢያት ጾም

ነቢያት እንዴት ለምን እንደጾሙ ለመግለጽ ቢያስፈልግ በብሉይ ኪዳን ሊቀ ነቢያት ሙሴ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ጹሞ መመሪያ ሕግ የሚሆኑ አሠርቱ ቃ ላትን ከእጊዜአብሔር ተቀብሏል ። ከዚ ህም ሌላ የእግዚአብሔር ወልድ ወደዚ ህ ዓለም መምጣት ተገልጾለት ትንቢት ተናግሯል ። ዘዳግም ፲፰.፲፱ ሌሎችም ነቢ ያት ነቢዩ ሙሴን መርህ አድርገው እያ ንዳንዳቸው ጹመዋል ። ዘርዝሮ ለመና ገር ስለሚበዛ በጥቂቱ ለመግለጽ ቢያስ ፈልግ ዳንኤልም እንደጾመ ሲአስረዳ በዚያ ወራት እኔ ዳንኤል ሳዝን ነበርሁ እንጀራም አልበላሁም ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም ብሏል ዳን ምዕራፍ ፲ ቁጥር ፪

ነቢዩ ኤልያስም እንደ ጾመና በጾሙ ም ወደ ብሔረ ሕያዋን እንደ ሄደ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል ፩ኛ/ ነገሥ ም. ፲፱.፰ እንግዲህ ነቢያት ጾሙ ስንልም ባቦታና በዘመን ተገናኝተው በአንድ ጊዜ ጾሙት ማለት ሳይሆን በእየዘመናቸ ው እንደጾሙ ታውቋል ።

ምክንያቱም ዘመን እያገናኛቸውም ና በመጾማቸውም እግዚአብሔር ጥበቡ ን ገልጾለቸው የራቀውንም አቅርበው በማየት ብዙ ትንቢት ተናግረዋል የት ንቢቱና የምሳሌውም ዓላማ ክርስቶስ ወ ደ ዓለም እንደመጣ በሥጋ ሰብእ እንዲ ገለጥና ፤ እንዲሞት በሞቱም ዓለምን እንዲአድን ከሙታንም ተለይቶ እን ዲነሣ ወደ ሰማይ እንዲያርግ ና ዳግመ ኛም ዓለምን ለማሳለፍ እንዲመጣ ነ በር ። በእግዚአብሔር መንፈስ ተቃኝ ተው ስለተናገሩት ያልተፈጸመና የማይ ፈጸም ትንቢት የለም የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነውና ።

በዘመነ ሊቃውንትም ፫መቶ አስራ ስምንት ሊቃውንት በፍትሐ ነገሥት በአንቀጸ ጾም ፲፭ አባቶች ነቢያት የጾ ሙትን መሠረት በማድረግ ከበዓለ ል ደት አስቀድሞ መንፈቀ ኅዳር ማለት ከ ኅዳር እኩሌታ ጀምሮ እንዲጾም ጽፈዋ ል ። ፋሲካውም በዓለ ልደት እንደሆነ ገልጸዋል ። በሌላ በኩል ግን የታሪክ መ ዝገብ በሆነው መጽሐፈ ሥንክሣር ያዕ ቆብያውያን ክርስቲያኖች ከኅዳር ፲፫ ቀን ጀምረው ይጾሙ እንደነበር ተጽፎ ይገኛል ።

በዘመነ ዮሐንስ ግን በኅዳር ፲፭ ጾመ ነቢያት ተጀምሮ በዓለ ልደት ታህሣሥ ፳፱ ቀን እንዲከበር ተገልጿል ። እንግ ዲህ ልናስተውለው የሚገባው ነገር ቢኖር ይህ ጾም የጌታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ የልደት መታሰቢያ ሲሆን በአንዳ ንድ ግለሰብ ዘንድ ምንጊዜም በአሥራ አምስት ይጀመራል ። ሌላው ደግሞ ም ንጊዜም በአሥራ ስድስት ይጀመራል። በማለት ልዩነት በመፍጠር ያለመግባ ባት ይታያል ።

እንዲህ ሊሆን አይገባም ለጾም ማድላ ት እንደሚገባ ተጽፎልና አብዝቶ መጾ ምም መላእክትን ያስመስላል ። እንዲ ያውም ለመብል ከመትጋት ለጾም መት ጋት የትሩፋት ዋጋ ያስጣልና ነው ። ስለ ዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ፫፻፲፰ ሊ ቃውንት በጉባኤ ኒቅያ በ፫፻፳፭ ዓ.ም ስለጾም የወሰኑትን ውሳኔ ተቀላላ መመ ሪያ በማድረግ ቤተ ክርስቲያናችን ለብ ዙዘመን ስትሠራበት ስታስተምርበት እንደኖረችና አሁንም በዚህ ሥርዓት ጸንታ እንደምትገኝ ግልጽ ነው ።

ይህ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሥርዓ ተ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ቀጥለው በተነሡት ሊቃውንተ ኒቅያ እንደተወ ሰነ በመጽሐፈ ሲኖዶስ ተገልጿል ። ወይም ፍትሐ ነገሥት ተብሎ የሚጠራ ው ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አስተካ ክሎ የሚናገረው መጽሐፍ ከመጻሕፍተ ሊቃውንት አንደኛው እንደሆነ ግልጽ ነው ።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊቃውንት በወሰኑት መሠረት ጾመ ነ ቢያትን መጾም እንዲገባ መገንዘብ ይኖ ርብናል ። ሐዋርያው ጳውሎስ በኋላ ዘ መን የሃይማኖት ልዩነት የሚፈጥሩ መ ናፍቃን እንዲነሱ አውቆ እኛ ካስተማ ርናችሁ ትምህርት ሌላ በድፍረት ያስ ተማራችሁ ሰው ቢኖር ይለይ ብሏል ። ገላትያ ምዕ.፩. ቁ.፱

የሐዋርያት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓቷም ሆነ እውነ ተኛ ሃይማኖት አንድ ነው ። በአንድ አምላክ ብቻ እናምናለንና የሃይማኖት ወፍራምና ቀጭን ፤ አይነትና ተወራጅ አይኖረውም እግዚአብሔር አምላክ እ ንዲያድን አውቆ ከልብ ማመንና በእም ነቱም ጸንቶ ሕጉንና ትእዛዙን መፈጸም ነው ።

በመሠረቱ ከላይ እንደተጠቀሰው ነ ቢያት በመጾማቸው መጻዕያትና ኃላፍ ያት ተገልጠውላቸው እውቀት ተሠጥቷ ቸው አማናዊ ትንቢት ተናግረዋል ። ም ሳሌም መስለዋል ፤ ሱባኤም ቆጥረዋል። ምንም እንኳ አረፍተ ዘመን ገትቷቸው በዓይነ ሥጋ ባያዩትም ተስፋውን ሰም ተው በትንቢት አይተውታል ። የትንቢ ታቸው መፈጸምም ነቢያትን ታማኞ ችና ጻድቃን ለመባል አብቅቷቸዋል ።

እንግዲህ እኛም ነቢያት የጾሙትን ጾም ብንጾም እግዚአብሔር ልመናችንን ይሰማናል ።ቅዱሳን ነቢያት የባህርይ ል ጅህን በሥጋ ልከህ አድነን ብለው እግ ዚአብሔር አብን በለመኑት ጊዜ ልመ ናቸውን ሰምቶ አንድ ልጁን በሥጋ ል ኮ አድኗቸዋልና ።

ስለዚህ የክርስቶስ ልደት መታሰቢያ የሆነውን የገናን ጾም በእየዓመቱ እንድ ንጾም ስለታዛዘን ትዕዛዙን ከሥራ ላይ አውለን ፍጹማን ክርስቲያኖች እንድን ሆን እግዚአብሔር በረድኤት አይለ የን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ

# የክርስቲያን አምላክ ሰው ሆኖ መጣ

የክርስቲያን አምላክ ሰው ሆኖ መጣ

ይህንን የምስክርነት ቃል የተናገረ ችው አንዲት መበለት እንደሆነች በገ ድለ ጊዮርጊስ ተጽፎ እናገኘዋለን ።

መበለቷ ኑሮዋ ችግርና ጭንቀትን የተሞላ ነበር የትዳር ጓደኛዋ ቀደም ብሎ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ስለነ በር ብዙ ቤተሰብ አልነበራትም ያላት አንድ ልጅ ብቻ ነበር ።

መበለቷ የዓለማት ሁሉ ፈጣሪ የሆነ ውን እግዚአብሔርን ከልብ ስለምታ ምን ትእዛዙንና ሕጉን አክብራ በጾም በጸሎት ተወስና ከመኖሯም ሌላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ያደረገውን ተጋድሎና ከክርስ ቶስም የተቀበለውን ቃል ኪዳን በመረ ዳት በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ አምላ ክ ትማጸን ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ይረዳኛል ይጠ ረኛል ይቀብረኛል ብላ ተስፋ የምታደ ርገው ልጅዋ ሞተባት መበለቷ ያንን አንድ ልጅዋን በማጣቷ እጅግ በጣም ምርር ያለ ልቅሶ ስታለቅስ ቅዱስ ጊዮር ጊስ ሰውን መስሎ መጣና አይዞሽ አት ዘኚ ልቅሶሽን ወደ ደስታ መልሽ ይህ የሞተው ልጅሽ አሁን በቅጽበት ተነ ሥቶ ከአንቺ ጋር ይኖራል አላት ።

መበለቷ ግን የቅዱስ ጊዮርጊስ ቃል እውነት ስላልመሰላት እንደፌዝ ትቆጥ ረው ጀመር ሰማዕቱ ግን ያለው አል ቀረም በሰማዕቱ በቅዱስ ጊዮርጊስ ጸሎ ትና ምልጃ ልጅዋ ወዲያውኑ ዳነ በተ ጨማሪም ቅዱስ ጊዮርጊስ በጸሎት የደ ረቀውን የቤቷን ምሰሶ አለምልሞላ ታል ።

በዚያን ጊዜ መበለቷ ቅዱስ ጊዮርጊስ በጸሎቱ ያደረገላትን ተአምር ተመል ክታ እጅግ በጣም ተደነቀች ምክንያ ቱም ምድራዊ ሰው ይህንን ዓቢይ ተአ ምር በጸሎቱ ያደርጋል ብላ አልገመተ ችምና ነው ከዚህም የተነሣ ነበር የክር ስቲያን አምላክ ሰው መስሎ ወደ እኔ መጣ ስትል አድናቆቷንና ያላትን አስ ተሳሰብ የገለጸችው ።

ቅዱስ ጊዮርጊስም የመበለቷን ቃል ሰምቶ መልስ ሲሰጥ እኔ አምላክ አይደ ለሁም የአምላክ አገልጋይ ነኝ እንጂ ብሏል ።

በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት የተፈ ጸመው ተአምር ይህ ብቻ ሳይሆን ሌሎ ችም አያሌ ተአምራት ተፈጽመዋል ። አሁንም ይፈጸማሉ ። ወደፊትም እስከ ኅልፈተ ዓለም ድረስ የሚፈጸሙ መሆ ናቸው የሚያጠራጥር አይደለም ።

በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም ቀደም ሲል ከተፈጸሙት ተአምራት አንዱን ተአ ምር እንመልከት በዘመኑ ያላመኑ ሰዎች ኃይል ያገኙበት በክርስቶስ ያመኑ ሰዎ ች የደከሙበት ዘመን ነበር ። በዚያን ዘ መን ብዙ ክርስቲያኖች ተገድለዋል ብዙ አብያተ ክርስቲያናትም በእሳት ተቃጥለዋል ።

በዚያው ወቅት በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የታነፀች አንዲት ቤተ ክርስቲያን ነበረችና በእሳት ቢያያይዟት አልቃጠ ልም አለች ። በእጅም ለማፍረስ ቢሞ ክሩ አልፈርስም አለቻቸው።በዚያን ጊዜ አዛዥ ለነበረው አውሄወስ ተብሎ ለሚጠራው መኰንን አንዲት በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም የታነፀች ቤተ ክርስቲ ያን በእሳት ብናያይዛት አልበላት አለ እኛም ለማፍረስ ብንሞክር አልፈርስ ልን አለች ብለው ነገሩት ። አውሄወስ የተባለውም መኰንን እጅግ በጣም ተና ደደና አሽከሮቹን ሰብስቦ ይዞ ሄዶ በሉ ከዚህ ላይ አፍርሱ ይህንንና ያንን በመ ዶሻ በሉት እያለ በዘንጉ እየጠቆመ ሲያ ስፈርስ የቀንዲሉ ሰባሪ ወርዶ መኸል ራሱን በጥብጦ ጣለው ወዲያው አእም ሮውን እጥቶ ሞቷል ቤተ ክርስቲያኗም ሳትፈርስ ቀርታለች በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም ልዩ ልዩ ተአምር በማድረግ ብዙ ጊዜ መኖሯን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይነግረናል ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ በዚህ ዓለም ብዙ ዘ መን አልኖረም ጠቅላላ ዕድሜው ሃያ





www.ethiopianorthodox.org

ሰባት ዓመታት ነው ። በእነዚህ ዓመታት መልካም ሥራ ሠርቶባቸዋል ፤

በተለይ በሰባቱ ዓመታት ወንጌልን ተግቶ በማስተማሩ ብዙ ፈተናዎች ደርሰውበት በትዕግሥት አሳልፎአቸዋል ፈተናውን ከአለፈ በኋላም ሰባት የብርሃን አክሌላት ለመቀዳጀት በቅቷል ።

እግዚአብሔርን አምነው የወንጌልን ቃል መሠረት በማድረግ የሚሠሩ ሁሉ ክርስቶስ ያደረገውን ተአምር ለማድረግ አያቅታቸውም ይህንንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር “እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ፤ ከዚህም የበለጠ ያደርጋል” ብሏል ዮሐ. ፲፬ ፲፪ ።



ቅዱስ ጊዮርጊስ ደራጐንን በጦር እንደወጋው

ክርስቶስ “ወደ ጠባብ በር ግቡ” እያለ ያስተማረውን ቃል መሠረት በማድረግ ሰማዕታት ወንጌልን በማስተማር ደማቸውን አፍሰዋል አጥንታቸውንም ከስክሰዋል ።


በአላውያን አደባባይ ቆመው ተገርፈዋል ተገፈዋል ተወቅሰዋል ተከሰዋል ።

በተቀበሉትም መከራ የተማጸነባቸውን ሰው ሁሉ ከመከራ ነፍስ እንደሚያድኑ ቃል ኪዳንን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀብለዋል ሰማዕታት በደማቸው ቅዱሳን በገድላቸው መላእክት በተራዳኢነታቸው የሰው ልጆችን ስለሚረዱ እኛም እናከብራቸዋለን ።

ስማቸውንም እየጠራን እንማፀንባቸዋለን ግን ሰማዕታትንየምናከብራቸው በግል ስሜት ሳይሆን የክርስቶስን ቃል በሚከተል መንፈሳዊ አመለካከት ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ ብሎ በሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት የሰማዕታትን ተራዳኢነት በማመን ለስማቸው መታሰቢያን እናደርጋለን ።

መታሰቢያቸውንም ከምናደርግላቸው ቅዱሳን ሰማዕታት አንዱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ነው ። በእግዚአብሔር አምነን በቅዱስ ጊዮርጊስ በመማፀን የምናቀርበው አገልግሎት ሁሉ የሠመረ ይሆንልን ዘንድ የክርስቶስ ፈቃዱ ይሁንልን ።

ሊቀ ል. ነቅዓ ጥበብ ወንድም







# ዜና ሊቃውንት

## የመጋቢ. አስፋው አጭር የሕይወት ታሪክ

መጋቢ. አስፋው መኮንን በውሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ገነተ ማርያም ደብር ከአባታቸው ከአቶ መኮነን ወልዱ ከእናታቸው ከወ/ሮ ሁሉ ሀገርሽ በ፲፰፻፹፫ ዓ/ም መጋቢት ፳ ቀን ተወለዱ በ፷ ዓመታቸው ከአባ አርከ ድንግል ንባብና ዳዊት ከቃል ትምህርት ጋር ተማሩ ቀጥለውም በዚያችው ደብር ከመሪጌታ አውራሪስ ጸዋትወ ዜማን አ



መጋቤ አስፋው እኒህ ነበሩ

ጠናቀው ተማሩ ከዚያም ዲያቆን ሁነው በተወለዱበት ደብር ይቀድሱ ጀመር ከዚያም በዚሁ አውራጃ ውስጥ ግደን ወረዳ እየላ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ከአለቃ ቀጸላ ዝማሬ መዋሥዕት ተምረው እንዳበቁ ወደ ዋድላ ሄደው የነጃ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ከመሪጌታ ነቅዓ ጥበብ ቅኔ ከነአገባቡ በደንብ ተምረው ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ ተወለዱበት ደብር ገነተ ማርያም ተመልሰው በሕግ ሚስት አግብተው ዝማሬ መዋሥዕት ለ፬ ዓመት ያህል እንዳስተማሩ የሕግ ሚስታቸው ስለሞቱባቸው ወደ ዋግ ሰቆጣ ሔደው ከአለቃ ንዋየ ክርስቶስ የ፬ቱ ወንጌል ትርጓሜንና የውዳሴና የቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ ተምረው ለምንኩስናሲዘጋጁ ወደ ዓለም ገብተው ልጅ እንደሚወልዱ በራእይ ነግሯቸዋል ። ከዚያም በድጋሜ ወደተወለድክበት ደብር እንድትመለስ የሚል የተደጋጋመ ሕልም ስለ አዩ የምንኩስና ዝግጅታቸውን አቁመው ከታወቁት ሊቅ ከአሊቃ ዓለሙ ከብሴ ዘንድ ወይብላ ደብር ድጓ በሚገባ ተምረው ሲዘልቁ ሰቆጣ የነበሩት ዋግ ሹም ከበደ ኃይሉ ካባ ሸልመዋቸዋል ። ከዚያም ወደቤተልሔም ሔደው ድጓ አስመስክረው የድጓ መምህር ሁነዋል ። ቀጥለውም ወደዋግ ሰቆጣ ተመልሰው የአቋቋም ትምህርት ከአሊቃ ክንፉ መብራቱ በሚገባ ተምረው እንደጨረሱ ወደተወለዱ ባት ደብር ገነተ ማርያም ተመልሰው ድጓ እያስተማሩ በተጨማሪም የገነተ ማርያም መሪጌታ ሁነው ይሠሩ ጀመር መጋቢ. አሰፋው ድምፀ መልካምና ግርማ የነበራቸው ትጉህና ንቁ እንደመሆናቸው መጠን መቋሚያቸውን ይዘው ሲዘሙ ጸናጽላቸውን ይዘው ሲጸነፅሉ ለተመለከታቸው ሁሉ መልአክ ይመስሉ ነበር በዚህም ተወዳጅነታቸው ከአቡነ ይስሐቅ ካባ ተሸልመዋል ከደጃዝማች ወንድወሰንና ከደጃዝማች አስፋው ወሰንካሣም ካባ ከነቀሚሱ ተሸልመዋል። ከአባ ጸበሎ የብር መቋሚያ ከካባ ጋር ተሸልመዋል ።

በዘመኑ ከነበሩት ንጉሥም ጥንግ ድርብ ከካባ ጋር ተሸልመዋል ። መጋቢ. አሰፋው መኮንን የመምህራን እንደራሴ እየሆኑ ብዙ ትሩፋት ሠርተዋል በሌላም በኩል የብርና የሀል ሀብታም ስለነበሩ ዘር ላጣ ገበሬ ዘር የሚነግድበት ለቸገረው ነጋዴ ብር እያበደሩ የሀገሬው ሕዝብ አገልጋይ ነበሩ በየከብረ በዓሉም ከቤተ ክርስቲያን እየተገኙ ማኅሌት ሲቆሙ ሁሉም የእሳቸውን ዝማሜናጸናጽል ሽብሸባና እንቅስቃሴ እየተመለከተ ይደሰት ነበር ። ለምሳሌ በጦር ሜዳ የተሰለፈ ጀግና ግዳጁን ሲፈጽም ወኔ እንደሚሰማው መጋቢ. አስፋውም በመንፈሳዊ አገልግሎት ተመስጦ ስለነበራቸው በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነት ነበራቸው ። ጠቅላላ ዘመናቸውን ሲኖሩ ድጓ ከማስተማር ያቋረጡበት ጊዜ አልነበረም በዚሁም ትጋታቸው ብዙ ደቀመዛሙርትን አፍርተው ለቁም ነገር አብቅተዋል ። ከደቀ መዛሙርቶቻቸውም ውስጥ ጳጳሳትና የደብር አለቆች የሆኑ ብዙ ናቸው መጋቢ. አስፋው መኮንን በላስታ አውራጃ ለሚገኙ ሊቃውንትና ካህናት ታላቅ ሞገስ ነበሩ ።

ዝማሬውንም ሆነ ድጓውን የሚመሩትና የሚቃኙት በቃል ነበር እንጂ የድጓ መጽሐፍ ተመልክተው አያውቁም በዚህም ድጓ በጉንጬ የሚባል የቅጽል ስም ወጥቶላቸው ነበር ። ስንክሣርም ሆነ ሌላ የሚነበብ ነገር የቀረበላቸው እንደሆነ ሁሉንም ነገር በቃል የሚያነቡ ይመስሉ ነበር ።

መጋቢ. አስፋው መኮንን በደብረ ሮሃ ቅዱስ ላሊበላ በየዓመቱ ለንግሥ አይለዩም ነበር ለገና ለልደት የኢትዮጵያ ምእመናን በዓሉን ለማክበር ሲመጡ በላሊበላ ቤተ ማርያም ማሚጋራ ላይ ከመዘምራኑ ጋር ሲያሸበሽቡ ሁሉም ተመልካች የሚመለከተው መጋቢ. አስፋውን ነበር በይበልጥ የጐንደርና የጐጃም ሊቃውንት የላስታን ሰው ባገኙ ቁጥር የሊቁ መጋቢ. አስፋውን ደኅንነት ሳይጠይቁ አያልፉም ነበር መጋቢ. አስፋው መኮንን አርቀው ተመልካች ጾምና [illegible] አዘውታሪ ቅንዓት ምቀኝነት የሌለባቸው በአንደበታቸው ውሸትንና ሽንገላን የማያውቁ እውነተኛ ሊቅ



www.ethiopianorthodox.org

ነበሩ ፤ መጋቢ አስፋው ከትንሹ ከትል ቁ መግባባት የነበራቸው ኩራትና ትዕቢት የማይወዱ ጥንታዊ ባህላቸውን የማይለውጡ ታላቅ ሰው ነበሩ ለምሳሌም ያህል የኢትዮጵያ ቁሪዝም ኰሚሽን የጥንታዊ አለባበሳቸውን በመመልከት ደስ ስለአለው ገነተ ማርያም ቅጽር ግቢ መንፈሳዊ ጸሎታቸውን ሲያደርሱ በቁመታቸው ላይ እንዳሉ ፎቶግራፍ አንስቶ በከለርና በክልሽ አሳድጎ ቁመቱ አንድ ሜትር ጐኑ የሜትር ግማሽ የሆነ የፎቶ ግራፍ ሥዕላቸውን በደንብ አውጥቶታል ።

መጋቢ አስፋው መኮንን በሥጋ ወደሙ የተወሰኑ ደግ ሰው ነበሩ ፴፮ ዓመት በመማር ፴ ዓመት ድጓ በማስተማር እስከ ሕይወት ፍጻሜያቸው ሠርተው በተወለዱ በ፹፯ በሰማንያ ሰባት ዓመታቸው ገነተ ማርያም ደብር ላይ በሺ ፲፱፻፶፱ ዓ-ም መጋቢት ፳፬ ቀን አርፈው ብዙ ሊቃውንትና ምእመናን በተገኙበት በሕይወታቸው ባሰሩት መቃብር ቤት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞአል ።

አትራቢ አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ

# ከኢትዮጵያ ቅዱሳን ታሪክ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ቅድስት ሀገር እንደመሆኗ መጠን በውስጧም በርካታ ቅዱሳን ይገኙበታል ፤ በየገዳማቱና አድራባቱ የሚገኙትን ጥንታውያን መጻሕፍት ስንመለከት መጻሕፍትን ለማይመለከቱ አንዳንድ ሰዎች ታሪካቸውና ስማቸው እንግዳ የሆነ ደጋግ አበው ጻድቃን እናገኛለን የእነርሱን ታሪክ ለማጥናትና በሕይወተ ስጋ ሳሉ በሥሯቸውም መንፈሳውያን ስራዎች ለመጠቀም እንድንችል ታሪካቸውን በቅደም ተከተል እናቀርባለን በዛሬው ጽሑፋችን የምናቀርበው የጻድቁን አባ ዮሐኒን የሕይወት ታሪክ ነው ።

የአባ ዮሐኒ ትውልድ ሀገር በትግራይ ክፍለ ሀገር በተንቤን አውራጃ ሀገረ ሰላም ከተባለችው ቀበሌ ሲሆን የነበረው በ፲ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው ።

በዚያን ጊዜ ሥርዓተ ምንኩስና ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ገና ስላልገባ ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው ከሰው ተለይተው ግርማ ሌሊቱንና ድምፀ አራዊትን ታግሰው የሚኖሩ መናንያን ሁሉ የሚጠሩት ባሕታውያን እየተባሉ ነበር እንጂ አባ አይባሉም ነበር ባሕታዊ አምንዮስ በዚያን ዘመን ነበሩ የሚኖሩትም በቆላ ተንቤን ደብረ እንሣ ዓሣ ከተባለው በረሃ በጾም በጸሎት ተወስነው ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን በራዕይ የአባ ዮሐኒ መመረጥ ተገልጾላቸው ከሚጸልዩበት ቦታቸው ወጥተው ወደ ሀገረ ሰላም ከተማ ሄዱ ከዚያች ከተማ እንደደረሱ አንዲት ሴት ልጅ ወልዳ አገኙ ልጇም እጅግ በጣም ያማረ ነበር ሴቱቱም ሕፃኑን እየመገበች ለማሳደግ የማትችል ችግረኛ መሆኗን ለባሕታዊ አምንዮስ ስለነገረቻቸው ሕፃኑን ከእናቱ ተቀብለው ይዘው ወደ በዓታቸው ደብረ እሣ እንሣ ተመለሱና በሚፀልዩበት አጠገብ ከገደል ስር ድንጊያ ፈል - ፍለው መከደኛ አበጅተው ሕፃኑን [illegible] አስገቡና ገጥመውት ሄዱ ከበዓታቸው ጸሎታቸውን ፈጽመው ሕፃኑን ለማየት ቢሄዱ ቶራ ገብታ ሕፃኑን ስታጠባው አገኙ በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ አድንቀው ረዳቸው አበይዶ ይባል ነበር እርሱን ጠርተው ለዚህ ሕፃን ምግብ

ከእግዚአብሔር ታዝዞለታልና አንተ ሰውነቱን እያጠብክ ጠብቀው አትለየው ብለውት ሲያበቁ ባሕታዊ አምንዮስ ወደበዓታቸው ተመለሱ ።

ሕፃኑ አባ ዮሐኒም አደገና ለትምህርት ሲደርስ መንፈሳዊ ትምህርትን ከባሕታዊ አምንዮስ በሚገባ ተማረ ከዚያ በኋላ በጾም በጸሎት በስግደት ተወስኖ የሚኖር መንፈስ ጠንካራ ባሕታዊ ሆነ በጸሎትናበትሩፋቱም ድውያንን የሚፈውስ የዕውራንን ዓይን የሚያበራ ፤ ለምፅ የሚያነፃ ስለሆነ ብዙ በሽተኞች ወደእርሱ እየመጡ ይፈወሱ ነበር ።

አባ ዮሐኒ ውዳሴ ከንቱን የማይሻና ደግነቱንም ሰው እንዲያውቅበት የማይፈልግ ነበርና ከሰው ተለይቶ ድምፀ አራዊትንና ግርማ ሌሊትን ታግሦ ለመኖር ወደበረሃ ሂዶ ተጋድሎውን ቀጠለ ።

ወላጅ እናቱ ዜናውን ስምታ መጣችና በሚጸልይበት ዋሻ ፊት ለፊት ቆማ ሦስት ጊዜያት በማጨብ ጨብ ጠራችው እርሱም ብቅ ብሎ አይቶ የሴት መልክ አይቶ ስለማያውቅ በጣም ደነገጠና ፊቱን ወደገደሉ መልሶ ይጸልይ ጀመር ።

ወዲያው አጠገቡ የነበረው ገደል ተናደ ገደሉም በተናደ ጊዜ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ መጥቶ ወሰደና ብሔረ ሕያዋን እንዳስገባው መጽሐፈ ገድሉ ይናገራል ይህም የሆነው ኅዳር ፭ ቀን ነው ያን ጊዜ አባ ዮሐኒ ዕድሜው ፴ ነበር ።

በአባ ዩሐኒ ጊዜ የተናደው ገደል አሁንም ስለሚገኝ አንዳንድ ታሪክ ተከታታዮች ሰዎች እየሄዱ ይጐበኙበታል ገደሉም ሲናድ የተሠወረ ቤተ ክርስቲ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



# የሴቶች ዓምድ

## ቅድስት ሐና

"መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን ክፉ ዛፍም ክፉ ፍሬን ያፈራል እንጂ ከመልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ከክፉ ዛፍም መልካም ፍሬ ከቶ አይገኝም ።

ይህንንም በማስመልከት ቅዱስመጽሐፍ እንዲህ ይላል" ከእሾህ በለስ አይለቀምም ከአጣጥ ቁጥቋጦም ወይን አይቆረጡም ሉቃ. ፮ ፵፬ በማለት ጽፏል እንደዚህም ሁሉ ከመልካም ቤተሰብ የሚገኙ ልጆች በምግባር በሃይማኖት ያማሩ የስመሩ ልጆች ናቸው ይሁንና በዚህ ጽሑፋችን ልናሰፍረው የፈለግነው ስለ ልጅ አስተዳደግ ሳይሆን ስለ ቅ/ሃና የሕይወት ታሪክ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ስለ ቅ/ሃና እንዲህ ሲል ያብራራል ።

ቅ ሃና ሃይማኖታቸው ከፀና ምግባራቸው ካማረ ከደግ ቤተሰብ የተገኘች ልጅ ናት አባቷ ትውልዱ ከካህኑ ከአሮን ወገን ነገዱም ከነገደ ሌዊ ነው ። ይህም ደግ ሰው ሦስት ሴቶች ልጆች ነበሩት እነርሱም ፩ኛ የመጀመሪያዋ ማርያ ፪ኛ/ ሦፍያ ፫ኛ ሐና ይባሉ ነበር ።

ታሪኩን ከሦስተኛው ልጅ እንጀምርና ሦስተኛዋ ልጅ ቅ/ሃና ለአቅመ ሔዋን ስትደረስ ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ የሚሆን ኢያቄም የተባለውን ደግ ሰው አገባች በዚህን ጊዜ ሃና ምንም እንኳን ኢያቄምን እንዳገባች ለብዙ ጊዜ ልጅ ባለመውለዷ ብታዝንም ጥዋትና ማታ ተስፋ ባለ መቁረጥ ልጅ እንዲሰጣት ወደ ቤተ እግዚአብሔር እዘውትራ በመሄድ ፈጣሪዋን ደጅ ትጠናና ጸሎትም ታደርግ ነበር ።

እግዚአብሔርም የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ ፈጣሪ ከመሆኑም በላይ በንፁህ ልቦና በትሁት ህሊና ለሚለምኑት [illegible] ሰሚ ስለሆነ ከልብ በመነጨ እውነተኛ ጸሎትና ልመና አማካይነት ለዓለም ሁሉ ተስፋ መድኅኒት የሆነችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን እንድትፀንስ በምህረቱ ጐብኘት ፀነሰችም ።

የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍትና ሊቃውንቶቻችንም ቅ/ሃና እመቤታችን በፀነሰችበት ወቅት ብዙ ድንቅ ሥራዎች ይታዩ እንደነበር ይመሰክራሉ በዚያን ጊዜ ከታዩትም ጥቂቶቹን ሲጠቅሱ ፩ኛ/ ቤርሳቤህ የምትባል አንድ አይኗ የጠፋ አክስት ነበረቻት ይህችም ሴት ሃና እኮ ፀነሰች የሚል ወሬ ስትሰማ ብዙ ጊዜ ሃና ባለመውለዷ ታዝን ስለነበረች በጣም ተደስታ በጀሮዋ የሰማችውን



ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

በአይኗ ለማረጋገጥ እየገሰገሰች ወደሃና ትሄድና ሃናን እኔ እስከ ዛሬ ድረስ ልጅ ባለመውለድሽ በጣም ሳዝን ነበር ዛሬ ግን እግዚአብሔር በፈቃዱ ጐብኝቶሻል መሰለኝ ከንፈርሽ ደርቋል ጡትሽም ጠቁሯል እያለች ሰውነቷን ደሰስ አድርጋ እንዳበቃች ወዲያውኑ ሳታውቅ አይኗን ስትይዝ የጠፋው አይኗ በራ ይህንንም የተመለከቱ ሕዝብ በአድናቆት እፁብ ብለው አመስግነዋል ።

፪ኛ/ የአጐትዋ ልጅ ሳምናስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ እጅግ ትወደው ነበርና የአልጋውን ሽንኮር ይዛ እየዞረች ስታለቅስ ድንገት ጥላዋ በአስከሬኑ ላይ ቢያርፍበት ብድግ ብሎ ተነስቶ "ሰላም ለኪ እመሄውቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ" "ሰማይና መሬትን እስከነልብሱ ለፈጠረ ሰማያዊ አምላክ አያት የምትሆኚ ሐና ሆይ ሰላምታ ይገባሻል "ብሎ የአምላክ እናት የምትሆን እመቤታችን በማህፀንዋ ተፀንሳ እንዳለች መስክሮ ተመልሶ አርፏል ሲሉ ይናገራሉ ።

ይህንንም ድንቅ ሥራ የተመለከቱ አይሁድ ሃና ገና ሳትወልደው በፅንሱ ይህንን ሁሉ የሠራ ሲወለድ ምን ይሠራ ይሆን ካሁኑ ሃናን ከገጸ ምድር ማጥፋት አለብን ብለው ሲያድሙ እግዚአብሔር ካልጠላ የሰው ጉራና ፉከራ ከንቱ ስለሆነ ምንም ሳያደርስባት እርሷም እምነቷን በእግዚአብሔር ላይ ስለጣለች በምቀኝነት ከተነሳሱባት አይሁድ እግዚአብሔር ለይቶ ሊባኖስ ወደተባለው ቦታ ሄዳ እንድትወልድ እንዳደረገ ይተርካሉ

ይሁን እንጂ ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪኩን ብናስታውስ ይህ ደግ ሰው ማጣት ሦስቱም ልጆች ጻድቃኖች እንደነበሩ እንረዳለን ምክንያቱም የመጀመሪያዋ ልጁ ማርያ ለአቅመ ሔዋን እንደደረሰች ተድራ ባል አግብታ/ ሰሎሜን እንደወለደች ሲያብራራ ሰሎሜም እመቤታችን ቅድስት ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስትወልድ የተቀበለቻት መሆኗን ይገልጻል ። ፪ኛ/ ሶፍያም ባል አግብታ ኤልሣቤጥን ወለደች ኤልሣቤጥም የዮሐንስ መጥምቅ እናት መሆኗ ነው እንግዲህ እነዚህ ሦስቱም እህትማማቾች የበቁ ልጆችን ወልደዋል ። ሌላው ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የተገኘው እንዲህ [illegible] ኢያቄም ወሃና ወለዱ ሰማየ ሰማያውያ አሥረቀት ፀሐየ" ኢያቄምና ሐና ሰማይንወለዱ የወ

ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብእ ዓምድ

## የተቀደሰ ጋብቻ

ቅዱስ መጽሐፍ የተቀደሰ ጋብቻን በተለያዩ ምዕራፎች ሲያመሰግነው እ ናገኘዋለን ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደዕብራውያን በጻፈው መልእክት በ ምዕራፍ ፲፫ ቁጥር ፬ ላይ "መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ነው" ይልና "መኝ ታውም ንጹሕ ይሁን" ይላል ።

በቦረና አውራጃ በሳይንት ወረዳ ልዩ ስሙ ደልደሌ ከተባለው መንደር ተ ወለደ ።

የዕድሜ ገደቡ ለትምህርት ሲያ ደርስ በአጥቢያው በሚገኘው ወ ረሀይ ቅዱስ ሚካኤልና ደፈር ጊዮርጊ ስ በተባሉ አብያተ ክርስቲያናት የመ ጀ ደብረ ሲና ማርያም በተባለችው ደብ ር ፀዋትወ ዜማና መዝገበ ቅዳሴ ተም ሯል ።

በዚሁ እውቀቱ ወደ ተወለደበት ሀ ገር በመመለስ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ እስከ ፲፱፻፶፱ ዓ/ም መጨረሻ ቆ ይቷል ።



ዲ/ ጥበቡ ስጦታውና ወ/ት ገቢያነሽ ንጋቱ

ይህን ዓላማ መመሪያ በማድረግ ዲያ ቆን ጥበቡ ስጦታውና ወ/ት ገቢያነሽ ንጋቱ ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋ ወደሙ በመንበረ ልዑል ቅዱስ ማርቆ ስ ቤተ ክርስቲያን ፈጽመዋል ።

ዲያቆን ጥበቡ ስጦታው ከአባቱ ከአቶ ስጦታው ሺበሺና ከእናቱ ወይዘሮ ዘሪቱ ታረቀኝ በወሎ ክ/ሀገር ጀመሪያውን የንባብ ትምህርትና የዲቁ ና ቅስም ተምሯል ።

ከዚህ በኋላ የዲቁናን ሥልጣን ከብ ፁዕ አቡነ ገብርኤል ተቀብሎ በነዚሁ አድባራት በዲቁና ማዕረግ አገ ልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ መንፈሳዊ ትምህርቱን ለማጠናከር ወደ ጐንደር ክፍለ ሀገር በመሔድ በጋይንት አውራ

ዲያቆን ጥበቡ ስጦታው በ፲፱፻፷ ዓ/ ም ወደ አዲስ አበባ በመምጣት በደብረ ሳላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲ ያን ሲያገለግል ባለው ቅን አስተሳሰብ ና አስተዋይነት ተመርጦ በወሎ ክፍለ ሀገር በአምባሰል አውራጃ ለምትገኘው ደብረ ክርቤ ግሼን ማርያም የመንገድ ሥራ ድርጅት በአ.አበባ ከሚገኘው ኮ ሚቴ በአባልነት በማገልገል ላይ ይገ ኛል ።

በአጠቃላይ ዲያቆን ጥበቡ ስጦታ ው የመንፈሳዊ አገልግሎት ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ መልካም ጠባ ይና ቅን አስተሳሰብ ያለው ካህን በመ ሆኑ በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ካህናት ዘንድ ተወዳጅነት ያለው ነው።

ወይዘሪት ገቢያነሽ ንጋቱም ከአባት ዋ መምሬ ንጋቱ ደስታና ከእናትዋ ወ ሮ ወርቅነሽ ሀብተማርያም በአርሲ ክፍ ለ ሀገር በጭላሎ አውራጃ በጢዩ ወረዳ በአሰላ ከተማ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. ተወለደ ች ዕድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ የንባብ ትምህርት ከተማረች በኋላ በጭላሎ ተራራ ፩ኛ ደረጃ ት/ቤት በመማር የ፪ኛ ደረጃ ትምህርቷን ጨርሳ በንግድ ሥራ ሙያ ተመርቃለች ።

ወይዘሪት ገብያነሽ ንጋቱ የካህን ልጅ በመሆኗ በመንፈሳዊ ዝንባሌዋ በደብረ ምፅላል ቅድስት ማርያም የሰ ንበት ትምህርት ቤት ለ፰ ዓመታት በ አባልነት አገልግላለች ዛሬም በመንበ ረ ልዑል ቅዱስ ማርቆስ የሰንበት ት ቤት በተቋቋመው የሆኅተ መንግሥተ ሰማያት የሰንበት ት/ቤት ሊቀመንበር በመሆን ታገለግላለች ።

ከዚህ ጋር በተማረችው ትምህርትና ባላት የንግድ ሥራ ሙያ በመንግሥት መ/ቤት ተቀጥራ ትሠራለች ፣ ያለችው በመንፈሳዊ ተልዕኮ በጋብቻ ዓለም በተክሊልና በሥጋ ወደሙ ተወስና ጥሩ ዜጋ ለመፍጠር በመሆኑ ለዚህ ለተቀደ ሰ ጋብቻ በሙሉ ደስተኛነት የካቲት ፳፯ ቀን ፲፱፻፸፭ ዓ/ም/ ከዲያቆን ጥበ ቡ ስጦታው ጋር የመሠረቱ መሆናቸ ውን ባቀረቡት ሪፖርት ለማረጋገጥ ተ ችሎአል ።

እኛም ጋብቻው የተቀደሰ በመሆኑ የተቀደሰ ፍሬ እንዲያገኙ እንመኝላቸ ዋለን ።

በለጠ አበበ

# ዜና እረፍት

ወይዘሪት ሙሉ ዓለም ተፈራ ከአባቷ ከሃምሳ አለቃ ተፈራ ጀምበሬ ፣ ከእናቷ ከወ/ሮ ኢየሩሴ ዓለሙ በጐጃም ክፍለ ሀገር በደብረ ማርቆስ ከተማ ኅዳር 22 ቀን 1953 ዓ.ም. ተወለደች ።

ወ/ት ሙሉዓለም ዕድሜዋ ለትምህ ርት በደረሰ ጊዜ በተክለ ሃይማኖት መ ለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ገብታ ከ1ኛ -8ኛ ተማረች ። ከዚያም ከ9ኛ - 12ኛ በድብዛ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ተከታትላ የ12ኛን ክፍል አጠናቃለች ።

ወጣት ሙሉ ዓለም ተፈራ በሕይወት በነበረችበት መዋዕለ ዘመኗ እንደ አንዳ ንድ ወጣቶች አንድ ጊዜዋን በአልባሌ ቦታ ሳታጠፋ በጐጃም ሀገረስብከት በ ደብረ ማርቆስ ከተማ በሚገኘው ሃይማ ኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቅ ማኅበራት አባል በመሆን ብዙ ክርስቲ ያናዊ ተግባራትን በማከናወን የተቀደሰ አገልግሎት አበርክታለች ። ከዚህም ው ስጥ በተለያዩ ጊዜያት በኃላፊነት ደረጃ በመመረጥ

ሀ/ በጸሐፊነት

ለ/ በገንዘብ ያዥነት

ሐ/ በፕሮግራም ኃላፊነት

መ/ በማኅበሩ የእጅ ሥራ ዘ ርፍ ውስጥ በመሥራትና ሌሎችንም በ ማበረታታት ለማኅበሩ ከፍተኛ አስተ ዋጽዎ አድርጋለች ።

እንዲሁም ሙሉዓለም በዚህ ብቻ ሳ ትወሰን በእመቤታችን ቅድስት ድን ግል ማያም ስም በተቋቋመው ማኅበር አባል በመሆን ለመንቀሳቀስ ለማይችሉ ና ለዕለት ምግባቸው እንኳ በአካላቸ ው ኮርተውና ሰርተው መመገብ ለማ ይችሉ አካለ ስንኩላንና ድኩማን ወገኖ ቻችን በዕለት ጉርስና በዓመት ልብ ስ በመርዳት፣ የቅዱሳት አንስትን ፈለግ ተከታይ ወጣት ነበረች ።ለዚህም ትታው ያለፋችው ስነ ምግባር የትሩፋት ሥራ ዋ ሕያው ምስክር ሆኖ ስሟን ሲያስጠ ራት ይኖራል ።

ማይምነትን ከምድረ ኢትዮጵያ ለማ ጥፋት በታቀደው አላማ መሠረት ይህ ችው ክርስቲያናዊት ወጣት በ1973 ዓ.ም. በደብረ ማርቆስ አውራጃ በጐዛምን ወረ ዳ በአባ ሊባኖስ ዐቢይ ጣቢያ ልዩ መጠ ሪያው ደንባ አባ በሚባል ቀበሌ ዘምታ ማይምነትን በመዋጋት ብሔራዊ ግዳጅ ዋን ተወጥታለች ። ወጣቷ በዘመቻ ላይ ሳለች በሥራ ትጋትዋና በምታሳየው ትሕትና በተማሪዎቿ ዘንድ ተወዳጅነ ትን አትርፋ ነበር ።



የወ/ት ሙሉዓለም ተፈራ ይህች ነበረች

ስለዚህም ታስተምረው የነበረው ሕ ዝብ በመልካም ክርስቲያናዊ አርያነቷ ከመወደዷ የተነሳ በስሟ ላይ "ዬ" ፊ ደልን በመጨመር ማለትም ሙልዬ በ ማለት ይጠሯት እንደነበር የቅርብ ጓደኞቿ ይመሰክራሉ ። ይህም ልጅቷ በቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ሥርዐት ተኮትኩታ ያደገች ፣ በግብረ-ገብ የታነ ፀች እግዚአብሔርን ፈሪ ፣ ትእዛዙን አ ክባሪ መሆኗን በጉልህ ያስረዳናል ።

ወጣትዋ ከላይ እንደተገለጸው ሊጋ ዕድሜዋን በሙሉ ከመንፈሳዊ ሥራዋ ጋር አጣምራ ኅብረተሰቡንም በስፋው አገልግላለች ። ይህም እናት ሀገሯን አፍቃሪ ፣ ለአንድነቷ ቀናዒ ፣ ለዕድገቷም ታታሪ መሆኑዋን ያስረዳል ። በመሆኑም ወጣቷ በነበረችበት ከፍተኛ 2 ቀበሌ 05 ውስጥ በልማት ሥራ በመሳተፍ በማስተማርና ሌላ ልትሠራው የሚገባ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የጤና ዓምድ

## የወባ በሽታ መከላከያ

የወባ በሽታ ለህመም ምክንያት የሚሆንና ለሞት የሚያደርስ በዓለም ላይ ከፍተኛ ደረጃ ከሚሰጣቸው በሽታዎች አንዱ ነው ።

ይህ በሽታ ጉሉ ሊደን የሚችል በሽታ ሰ... ...ነሽ የሚሆነውም አንድ ህዋስ (አንድ ሴል) ያለው እንስሳ ነው ። ይህ እንስሳ በጣም ትንሽ ከመሆኑም በ ላይ አጉልቶ በሚያሳይ መነፅር ካልሆነ በስተቀር በዓይን ለማየት አይቻልም ይህ የወባ ትንኝ በተለየ መንገድ ሊበዛ ይችላል ።

የወባ በሽታ ከአንድ ህመምተኛ ወደ ሌላ ህመምተኛ ሊተላለፍ ይችላል ። የሚተላለፈውም በወባ ትንኞች አማካይነት ነው ። የወባ ትንኞች የሰውነት ቆዳን በመንከስ በውስጣቸው ያለውን ፈሳሽ ወደ ሰውነት ውስጥ በማስገባት በሰውነታችን ውስጥ ለግማሽ ሰዓት ያህል ይሰራጫል ። ይህ የተበከለ ፈሳሽ የሚይዛቸው የወባ ጥገኞች ህዋሳቶችን ነው ። እነዚህ ህዋሳቶች ወደ ሰውነታችን ክፍሎች ይገባሉ ። ከዚህ በኋላ ከአምስት እስከ ሰባት ቀን ባለው ጊዜ በጉበት ውስጥ በመግባት ይባዛሉ ማለት ነው ። በሙቶ የሚቆጠሩ የወባ ጥገኞች ህዋሳቶች በደም ውስጥ ያሉትን ንጥረ ነገሮች በመመገብ ለመኖር ይችላሉ ።

የወባ ትንኞች በጥገኝነት በመኖርና በመመገብ ሙሉ እድገት ካገኙ በኋላ በአሥርና በሐያ ክፍሎች ይከፋፈላሉ ። እነዚህ የተከፋፈሉት ጉጂ ህዋሳቶች በ ሰውነት ውስጥ በሚገኙት ጠቃሚ ህዋሳቶች ላይ ጉዳት በማድረስ ህመምተኛው የመንቀጥቀጥና የብርድ ስሜት ይታይበታል ።

የወባ ህዋሳቶች በአራት ይከፈላሉ ። እነዚህ አራት የተለያዩ የወባ ጥገኞች የተለያየ አይነት ፀባይ አላቸው ። ነገርግን የእድገታቸው ሒደት የተመሳሰለ ነው። እነርሱም ፦

፩ኛ/ ፕላስሞድያም ቫይቫክስ
፪ኛ/ ፕላስ ሞድየም ማላርያ
፫ኛ/ ፕላስምድየም ፋልሲፓሪም
፬ኛ/ ፕላስሞድየም አቫል በመባል ይታወቃሉ ።

ፕላስሞድየም ቫይቫክስ ይህ ትንኝ ለመራባት አርባ ስምንት ሰዓት ብቻ ይወስድበታል ። የብርድ ስሜት በህመምተኛው ላይ ይታይበታል ።

ፕላስሞድየም ማላርያ ይህ ትንኝ ለማደግና ለመራባት ሰባ ሁለት ሰዐት ይወስድበታል ይህ ትንኝ በህመምተኛው ደም ውስጥ በገባ በአራተኛው ቀን ህመምተኛው የብርድና የመንቀጥቀጥ ስሜት ይታይበታል በተጨማሪም የሙቀት መጠን በጣም ከፍ በማለት ትኩሳትን ያስከትልበታል ።

ፕላስሞድየም ፋልሲፓሪም ይህ የወባ ትንኝ ከሃያ አራት ሰዓት እስከ ሰባ ሁለት ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ በሰውነት ውስጥ ገብቶ ሙሉ እድገቱ ሊገለፅ ይችላል ።

ይህ የወባ ትንኝ ከሌላው የወባ ትንኝ የተለየ ነው ። ምክንያቱም በጣም ሃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ እነዚህ የወባ ጥገኞች ህዋሳቶች በትንሽ ጊዜ ውስጥ በሰውነታችን ውስጥ ያለውን ደም ይበክሉታል ። በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ በሰውነታችን ዋና ክፍሎች ላይ ጉዳት ያደርሳሉ ። ለምሳሌ በጣፊያና በአጥንት ውስጥ በመግባት ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ ።

ፕላስሞድየም አቫል የተባለው የወባ ህዋስ ደግሞ ከላይ ከተጠቀሱት ጋር የሚመሳሰል ፀባይ አለው ።

በሕመምተኛው ላይ የሚታዩ ምልክቶች ፡

፩ኛ/ የደም ማነስ
፪ኛ/ የጣፊያ እብጠት
፫ኛ/ ትኩሳት
፬ኛ/ የብርድና የማንቀጥቀጥ ሁኔታዎች
፭ኛ/ ብዙ ላብ ማላብ
፮ኛ/ የራስ ምታት
፯ኛ/ የማቅለሽለሽና የማስመለስ ሁኔታዎች ናቸው ።

ህመምተኛው የያዘው የወባ አይነት በጣም ኃይለኛው ማለትም ፕላስሞድየም ፋልሲፓረም ከሆነ የሚያስከትልበት ጉዳት በጣም ከፍተኛ ነው ። ይኸውም የኩላሊት በሽታ የሆድ ሕመም የአእምሮ መታወክን ከማስከተሉም በላይ ራሱን በመሳት ወደሞት ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል ።

አንድ የወባ በሽታ የያዘው ህመምተኛ ህመሙ ሊታወቅለት የሚችለው በደም ውስጥ በሚገኙት የወባ ህዋሳቶች አይነት ነው ።

በደም ውስጥ ያሉትን የወባ ህዋሳቶች በመድኃኒት ማጥፋት ያስፈልጋል ። ህመምተኛው የራስ ህመም ስላለበት መድኃኒት ይሰጠዋል ።

ለትኩሳት የሚደረግለት ሁኔታ ትኩሳቱን ለማቀዝቀዝ በንጹሕ ጨርቅ ውሃ እየነከሩ በህመምተኛው ሰውነት ላይ በማድረግ ለህመምተኛው አስፈላጊ የሆነ እርዳታ መስጠት ነው ። ፈሳሽ ችን በብዛት እንዲወስድ ህመምተኛውን መገፋፋት በጣም አስፈላጊ ነው ።

የወባ በሽታን ለመከላከል የምናደርጋቸው ጥንቃቄዎች ፤

በዓለም ላይ የወባ በሽታ በአንዳንድ በተወሰኑ ቦታዎች ይገኛሉ ። የወባ በሽታን ለመቆጣጠር የሚያስችሉን የተለያዩ መንገዶች አሉ ። ከነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ አንድ የወባ በሽታ የተያዘ ሰው በ ህመምተኛው ደም ውስጥ እነዚህ የወባ ጐጂ ህዋሳቶች በጥገኝነት በብዛት ስለሚኖሩ እነዚህ ህዋሳቶች ከህመምተኛው ወጥተው ወደ ጤነኛ ህብረተሰብ የሚተላለፍበትን መንገድ ማስወገድ በጣም አስፈላጊ ነው ።

፪ኛ/ እነዚህ ህዋሳቶችን ለመከላከል የ ቤት ዕዳት በጣም አስፈላጊ ነው ።

፫ኛ/ የወባ ትንኞች ያሉበትን ቢቻል በ አካባቢ ማጥፋት የሚራቡበትን ውሃ የሚያርፉባቸውን ቦታዎች መድኃኒቶችን በመርጨት ጐጂ ህዋሳቶችን ማጥፋት በጣም አስፈላጊ ነው ።

፬ኛ/ በተጨማሪም በጉዞ ላይ መወሰድ የሚገባቸውና ከበሽታው ለመከላከል የሚረዱ መድኃኒቶችን መያዝ በጣም አስፈላጊ ነው ።

፭ኛ/ በአጠቃላይ የሰውነት የአካባቢ ንፅህና መጠበቅ ለወባ በሽታ መከላከያ አይነተኛ መሣሪያ ነው ።

ተማሪ ነርስ መንበረ ምህረቱ

## የኢትዮጵያ ቅዱሳን ....

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ያን ተገልጿል ። አሁን የቤተ ክርስቲያኑ ስም አባ ዮሐኒ ደብረ (ዓሣ) አንሣ ተብሎ ተሰይሟል ።

በዚያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ብዙዎች ግሁሣን ፣ ባሕታውያን ፣ ጻድቃን እንደሚኖሩበት ይታመናል ቤተ ክርስቲያኑ ዙሪያውን በዋሻ የተከበበ ሲሆን ላዩ ደጋ ነው የሀገሬው ሕዝብም ላይ ላዩን አያርሰውም ። ስለዚህም ብዙ የዱር አራዊትና እንስሳት ይገኙበታል ደብረ ዓሣ (አንሣ) እየተባለ የሚጠራውም የተንቤን ከፍተኛ ተራራ የሚገኘው ከላይ እንደተገለጸው ከቆላ ተንቤን በታች ጸጸራ ነው ፤ ተራራውም በጣም ከፍተኛነት ያለው ከመሆኑ የተነሣ ከተራራው ላይ ወጥቶ ሲመለከቱ የትግራይና የጐንደር ክፍላተ አገር በጠቅላላው ቁልጭ ብለው ይታያሉ ጥግ ጥጉም በነጫጭ ገደሎች የተሸለመ እጅግ በጣም ያማረ ተራራ ነው ።

ይህ ተራራ በጨለማ ሲያዩት እንደ ጨረቃ ያበራል በዙሪያውም ዋሾች በብዛት ይገኙበታል በዓቢይ ጾምና በፍልሰታ ምህላ ሲደርስ ማኅሌት ሲቆም ድምጹ ይሰማል ቦታው ግን የት ላይ እንደሆነ ለይቶ ለማወቅ የማይቻል መሆኑን በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ይናገራሉ በተራራው የሚገኘውም ዋሻ በምዕራብ ተከዜን ተሻግሮ እስከ ሰሜን ተራራ የሚደርስ ሲሆን በምስራቅ በኩል እስከ አዘሎ ተራራ የሚያደርስ የምድር ውስጥ የምድር መንገድ ያለው መሆኑን አንዳንድ አባውንት ይናገራሉ ።

ገድለ እለወጺፍ የሚባለው መጽሐፍ በዚሁ ዋሻ ውስጥ ለውስጥ ስላለው መንገድ ገልጸ ሲያበቃ ይኸውም መንገድ የቅዱሳን መገናኛቸው ነው ይላል የዛሬ ጽሑፋችን ከዚህ ላይ አቁመን በሚቀጥለው ጽሑፋችን ስለቤተ ክርስቲያኑ አሠራርና ስለተተከለበት ክፍለ ዘመን እንገልጻለን ።

መጋቤ ስብሐት መልኩ ፈለቀ የቤተ መጻሕፍት ሐላፊ

## ዜና ዕረፍት

ከገጽ ፲፮ የዞረ

ትን የወጣትነት ድርሻዋን በአ.አ..ወ.ማ አባልነቷ አበርክታለች ።

ወይዘሪት ሙሉዓለም ተፈራ ክርስቲያናዊ ተልዕኮዋን ትፈጽም የነበረው በአካባቢዋ ብቻ አልነበረም ፣ ከከተማ ወጣ ብለው በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናትም በመዘዋወር በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን አባቶችን እናቶችን መጠየቅና በሚያስፈልጋቸው መርዳት ከምትፈጽመው የተቀደሰ አገልግሎት አንዱና ዐቢይ ክፍል ነበር ።

ከደብረ ማርቆስ ከተማ በግምት 8 ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኘው በአባ አሥራት ገዳም ውስጥ የሚገኙትን መነኮሳት ጫካውና ገደሉ ሳያስፈራትና ሳይሰለቻት እየሄደች በመጠየቅ ፣ ለራሷም ትምህርት በማግኘትና አንስት መነኮሳትንም ፦ "አይዞአችሁ ፣ በርቱ ፣ አምላካችን በእውነትና በቅድስና ለምንሠራው ሁሉ የቅርብ ረዳታችን ነውና እምነታችሁ የማይፈነቅል ዐለት ይሁን" በማለት የምታጽናና መንፈሳዊት መልእክተኛ ነበረች ።

በቤተሰብም ደረጃ ወላጆቿን አክባሪ ፣ እኅቶቿን አፍቃሪ በመሆን መልካም ምሳሌነትዋን እንዲከተሉ በሥራም ሆነ በቃል ከማስረዳት ተቆጥባ አታውቅም ነበር ።

ነገር ግን " .... አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ ።" ላለው አምላካዊ ቃል መሠረት ወጣትዋ ወ/ት ሙሉ ዓለም በተወለደች በ22 ዓመቷ 21 ቀን 1975 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታለች ። ያረፈችውም ለሞት ካደረሳት ሕመም ጋር እየታገለች በእምነት ጸንታ በተለመደው መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ እንዳለች ነበር ። "... እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን ..."የሚለውን ፈጽማ በሰላም አንቀላፋች ። ደግሞም ፦ "... የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ፤" ይላልና ።

የወይዘሪት ሙሉ ዓለም በሞት መለየት ለቤተዘመድ ፣ ለጐረቤትና ለሃይማኖት አበው አባላት መሪር የሆነ የኃዘን ሰቀቀን ቢሆንም እስከመጨረሻው በእምነት ጸንታ የማይሞት ስነምግባርዋን ትታ በማለፏ እንጽናናለን ። ምንም እንኳ የሩቅ ዓላማዋ አብቦ ሳያፈራ ባጭሩ የተቀጨ ቢሆንም በጅምር ያለው ክርስቲያናዊ አገልግሎቷ ፈለጓን በተከተሉ እኅቶች አብቦ እንደሚያፈራ ጥርጥር የለውም ።

በመጨረሻም አጽናኙ አምላካችን የወጣትነት አበባዋ ስለረገፈባቸው ወላጆቿ ለቤተ ዘመዶቿ መጽናናትን እንዲሰጣቸው እንመኛለን ።

ሚናስ መንክር
ደብረ ማርቆስ ጐጃም




www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት


ግብርና ስለሚሰጠው በረከት በግብርና ሚኒስቴር በየወሩ እየታተመ በሚወጣው ዜና ግብርና መጽሔት አማካይነት በተለያዩ ርእሶች ለአንባብያን ይጠቅማሉ ተብለው ግምት የተጣለባቸውን ትምህርቶች አቅርበናል ።

በዛሬው ዝግጅት ደግሞ በእርሻ ሥራ ሁሉም ባለሙያ ይሆን ዘንድ ታስቦ በትምህርት ሚኒስቴር ገና በትምህርት ቤት ያሉ ተማሮች በዚህ ሥራ ልምምድ እንዲያደርጉ በትምህርትሚ ኒስቴር

<u>የጓሮ አትክልት ጥቅም</u> ፡

አትክልት በሳይንስ እንደሚነገረው ለሰውነታችን ቪታሚኖችንና ማዕድናትን ይሰጣሉ ፡ ስለዚህም አዘውትሮ አትክልትን የሚመገብ ቪታሚኖችንና ማዕድናትን በብዛት ስለሚያገኝ መላ ሰውነቱ በጤንነት ተጠብቆ ከመኖሩም ሌላ ብርታትንም ሊሰጠው ይችላል ።

በአጠቃላይም በመልካም ጤንነት ተወስኖ ለመኖር ሲያስፈልግ አትክልትን አዘውትሮ መመገብ አስፈላጊ መሆኑን በዜና ማሰራጫ በተደጋገመ ጊዜ




## የጓሮ አትክልት ለሰው አስፈላጊ ምግቦች ናቸው

የትምህርት መሣሪያዎች ማደራጃና ማከፋፈያ አገልግሎት "እርሻ" በሚል ርእስ መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል ።

ከነዚህ መጻሕፍት በአራተኛው መጽሐፍ ውስጥ ስለጓሮ አትክልት አጠቃቀምና ስለ ጥቅማቸው የተጻፉትን ለአንባብያን ስናቀርብ ካህናትም በዚህ የአሠራር ዘዴ ተጠቅመው ሌላውንም ለመጥቀም እንዲዘጋጁ ለማድረግ ነው ።

ተነግሮአል ። በተለይም ሕፃናትን በጥሩ ሁኔታ በጤንነት ለመንከባከብና ያለችግር እንዲያድጉ ሲያስፈልግ የተፈጨ የአትክልት ዓይነትን መመገብ ጠቃሚ ነው ።

የጓሮ አትክልት ስንል ተካዩ ወይም አልሚው ከላይ እንደተገለጸው በምግብነት ብቻ የሚጠቀምበት ሳይሆን በቂ ምርት በማምረቱ በዚህ ሥራ ላልተሰማሩ ሌሎች በላተኞች በመሸጥ ተጨማሪ ገቢ ያገኛል ።



በዚህ ዓይነት በጓሮ አትክልት በቂ ገቢ የሚያገኙ ሰወች አሉ ፡ እገሌና እገሌ ብሎ ለመዘርዘር ባይቻልም ለምሳሌ ያህል በከፍተኛ 13 ቀበሌ 08 እንደነ አቶ ዝማዬ አመነ የመሳሰሉ ታታሪዎች ከምግብ አልፈው በመሸጥ ጠቃሚ ገቢ እንዳገኙ ከዚህ ቀደም ሲል በመጽሔታችን በማውጣት ለአንባብያን አስተዋውቀናል ።

ይህ ብቻ አይደለም በሰበታ የጌቴሴማኒ ደናግል መነኮሳይያት በንቃትና በትጋት ከሚተክሉት አትክልት ከሰበታ አልፎ በአዲስ አበባ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ግቢ ለሠራተኞች ሲሸጥ ማየታችን ሌሎችን የሚጋብዝ በመሆኑ በምሳሌነት እንዲጠቀስ አስፈላጊ ሆኖአል ።

ስለዚህ በጥሩ ሁኔታ ሠርቶ አትክልትን መመገብና በመሸጥም በገቢው መጠቀም ብልህነት ነውና የጓሮ አትክልትን በመትከል በምግብነቱም ሆነ በገቢው ለመጠቀም መጣጣር የሁላችንም ተግባር ሊሆን ይገባል ።

<u>የጓሮ አትክልት አይነትና አጠቃቀማቸው</u> ።

ከጓሮ አትክልት ጥሩ ምርት ለማግኘት የተከሉን ዓይነትና የሚበላውም ክፍል የትኛው እንደሆነ ማወቅ ተክሉ ሊደረግለት ስለሚገባው እንክብካቤ የበለጠ ይረዳል ።

የጓሮ አትክልት ሲባሉ ብዙ ዓይነቶች ናቸው ፤ በአጭሩ ግን ቅጠላቸው ፡ አገዳቸው ሥራቸው ፡ አበባቸውና ፍሬአቸው የሚበላ የጓሮ አትክልቶች አሉ ።

ከእነዚህም የአትክልት ዓይነቶች በዝርዝር በየመልካቸው በማስቀመጥ እንያቸው ።

1. ቅጠላቸው የሚበላ ስላጣ ፡ ጐመን፡ ቆስጣ እስፒናች ወ.ዘ.ተ..........

2. አገዳቸው የሚበላ ቀይና ነጭ ሽንኩርት ፡ ባሮ ወ.ዘ.ተ. ...

3. ሥራቸው የሚበላ ካሮት ቀይስር ፡ ድንች ፡ ራዴሽ ሽንኩርት ፡ ባሮ ፡ ፉሮ ፡ ወ.ዘ.ተ.

4. አበባቸው የሚበላ አበባ ጐመን ፡ ብሮክሌ ፡ ወ.ዘ.ተ. ...

5. ፍሬአቸው የሚበላ ቲማቲም ፡ በርበሬ ፡ ፎሶሊያ ፡ አተርና ባቄላ ወ.ዘ.ተ.. ናቸው ።

እነዚህ ሁሉ በሀገራችን ሊበቅሉና ሊመረቱ ሲችሉ ለሀገራችንም ሕዝብ በምግብነታቸው የተለመዱና የተወደዱም ሲሆኑ በሀገራችን ቀደም ሲል ያል ተሞከሩና በምግብነት ያልተለመዱ ዛሬ ግን እየተተከሉና ለምግብነት እየተለመዱ የመጡ የአትክልት ዓይነቶችም አሉ ።

ችግሩ ግን ከእኔ ጀምሮ ጓሮ ሲኖረው ትርፍ ሰዓቱን ለጓሮ አትክልት ሥራ መሥዋዕት ለማድረግ የሚጥር ያለመኖሩ ጉዳይ ነው ፡ እንዲህ ከሆነ ሁሉም በጓሮ አትክልት ሥራ ልምድ ቢኖረው ቤተሰቡን በጤንነት ሊመራው ይችላል ።

በራሴ ያየሁትን ብቻ ለመግለጽ እፈልጋለሁ ። በየአደባባዩ ይሸጥ የነበረው የአትክልት ምርት ለሕፃናት ልጆቻችን የቱን ያህል የጤንነት ግንባታን እንዳስገኘላቸው ስለጓሮ አትክልት ጠቃሚነት ሌላ ምሳሌ አያስፈልገውም ።

ስለዚህ እገሌ ከእገሌ ሳይባል የጓሮ አትክልት ቦታ ያለው ሁሉ አትክልትን በመትከል በምግብነቱ ተጠቅሞ በገቢውም ቢጠቀም መልካም ነው ። ከሥሩ መደሰት ካልሰሩ ደግሞ መቸገር እንደማይቀር የታወቀ ነውና ሠርተን በላባችን ወዝ እንጠቀም ።

ሊቀ ካህናት በለጠ አበበ

# የባህል ዓምድ

በዚህ የባህል ዓምዳችን የልዩ ልዩ ብሔረሰቦችን ባህልና ይዘት ከባህል ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እናስተዋውቃችኋለን ።

ኢትዮጵያ ማለት አዲስ አበባና አካቢዋ ብቻ ሳይሆኑ በውስጧ የሚኖሩ የልዩልዩ ብሔረሰብባህሎች መኖራቸውን ልናውቅ ይገባናል ። ተራራዎቿና ኰረብታዎቿ ወጣ ገባዎቿና ጉራንጉሮቿ ፡ በዙርያዋና በመካከሏ ያሉቦታዎችና ሕዝቦቿ በተለያየ ክልል የሚኖሩ ሁሉ ሳይቀሩ ቀደም ብሎ በነበረው ሥርዓት ተረስተው ይኖሩ እንደነበር እናውቃለን ። ባህልና ጐሣ ቀርቶ ሕዝቡንና አካባቢውን እንኳ የሚያውቅ ቢኖር በዚያው ሕብረተሰብ መካከል የሚኖር ብቻ ነበር ለማለት ያስደፍራል አሁን ግን በመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት የሁሉንም ባሕል በመጠኑም ቢሆን ለማወቅ ተችሏል ።

በዛሬው ጽሑፋችን በአፋር ብሔረሰብና በአርጐባ ብሔረሰብያለውንየጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓት እናቀርብላችኋለን ።

<u>የጋብቻ ጥሎሽ በአፋር ብሔረሰብእ</u>

የአፋር ብሔረሰብእ አባላት የሚገኙ በምሥራቅ ይፋትና ጥሙጋ በተጉለትና ቡልጋ ፡በየረርና ከረዩ አውራጃ በአሰብ አስተዳደር ፡በምሥራቅ ትግራይና ኤርትራ ነው ።

የዚህ ብሔረሰብእ አባላት በብዛት ዘላኖች ሲሆኑ ኢኮኖሚያቸውም የተመሠረተው በከብት እርባታ ነው ።

በአፋር ብሔረሰብእ ወንዱ ለጋብቻ የሚፈልጋትን ልጃገረድ ከመረጠ በኋላ ያደረገውን የጀግንነት ሙያ በልዩ ልዩ መልክ ይገልጽለታል ። ለምሳሌ ታላላቅ አውሬዎችን ገድሎ እንደሆነ በገደለበት ጊዜ የነበሩትን ታማኝ አዳኞች ያስመሰክራል ። ከዚህ በቀር የግዳዩን ምልክት ይሰጣታል የገደለበትን የጥይት ቀለህ ጆሮዋ ላይ ያንጠለጥልላታል የጀግንነት ተግባር የሌለው ወንድ ሚስት ለማግኘት አይችልም ነበር ።

ዛሬ ግን እንዲህ ዓይነቱ አጉል ልምድ በሕግ በመከልከሉ የጀግንነቱ ተግባር በቅቢ በተካከረ ግልድምና በአራት ከብት ጥሎሽ ተለውጧል ። አንድ አዳልወንድሚስትሲያገባለልጅቷ፡ወላጆችማለትለአባትአንድ በቅቤየተነከረ ግልድምና አራት ወይም የበለጡ ከብቶችን ይሰጣል አብዛኛው የአፋር ጋብ



www.ethiopianorthodox.org

ቻ የሚፈፀመው በዘመዳሞች መካከል ነው ። ይህም የሚደረግበት ምክንያት ጕሳቸው ከሌላ ብሔረሰብ ጋር እንዳይቀላቀል ለማድረግ መሆኑ ይነገራል ።

የጋብቻ ጥሎሽ በአርጐባ ብሔረሰብእ

ይህ ብሔረሰብእ የሚገኘው በደቡባዊ ተጉለትና ቡልጋ ፤ በሰሜናዊየረርና ከረዩ አውራጃዎች ነው ። የዚህ ብሔረሰብእ አባላት ዋና መተዳደሪያቸውና የኢኮኖሚያቸው ምንጭ ንግድ ነው። በአርጐባ ባህል ሴቶች ትምህርት ቤት አይሄዱም ። እንዲያውም ትምህርት ቤትን ያባልጋል ብለው ያምናሉ ። የዚህ ብሔረሰብእ የሆኑ ሴቶች ከትልቅ እስከ ትንሽ በአካባቢው ከሚገኙ ቅጠላ ቅጠሎች ልዩ ልዩ መዓዛ ያላቸውን ሽታዎች ማዘጋጀት ይችላሉ ።

በአርጐባዎች ባህል የደረሱ ልጃገረዶችና ያገቡ ሴቶች ወደውጪ እንደልብ አይወጡም ቢወጡም ጥቁር ልብስ ለብሰውና ፊታቸውን በሻሽ ተሸፍነው ነው ። አንድ የአርጐባ ወንድ ለትዳር የመረጣትን ልጃገረድ ሊያገኝ የሚችለው በሽማግሌዎች አማካኝነት ነው ። አግቢው ወደመረጣት ልጃገረድ አባቷን እንዲለምኑ ሽማግሌዎች ይልካል ። በሽምግልናው ጊዜ ሽማግሌዎቹ ለልጅቱ አባት እጮኛው የገዛላትን ምርጥ ሽርጥ ይዘውላት ይሄዳሉ ሽምግልናው ከተሳካ እጮኛው በፍጥጥሙ ቀን ከብትና በርካታ ገንዘብ ለልጅቷ ወላጆች በጥሎሽ መልክ እንዲሰጥ ይገደዳል ። እንደተለመደው ለልጅቷ ልዩ ልዩ ጌጣጌጥና የገንዘብ ስጦታ እንዲሰጥም ይደረጋል። በሠርጉ ዕለት የልጅቷ አባት ከልጁ በተቀበለው የሠርግ መደገሻ ገንዘብ ለሠርገኞቹ ከፍተኛ ድግስ ይደግሳል እጮኛው በሠርጉ ዕለት ሁለት ለልጅቷ ልዩ ልዩ ጌጣጌጥና ሙሉ ልብስ ይዞ ይመጣል ። ሠርገኞቹና ሙሽራው ለአራት ቀናት በልጅቷ ቤት ይቆዩና በአምስተኛው ቀን እድምተኞቹ ወደ የቤታቸው ይመለሳሉ ሚዜዎችም ሙሽራይቱን ከወላጆቿ ዘንድ ትተው ከሙሽራው ጋር ወደየቤታቸው ይሄዳሉ ። ሙሽራይቱም አመት እስኪያልፋት ወይም እስከምትወልድ ከወላጆቿ ቤት አትወጣም ። ባልዋም ወደ እሷ ሲመጣ አማቾቹና ዋርሶዎቹእንዳያዩት ይሸሸጋል ምክንያቱም በባህላቸው አማች በጣም ይከበራልና ነው ።

# ሰባክያንና ተግባራቸው

በዓለም ውስጥ የክርስቶስን ቃል ለ ምዕመናን የሚአሰራጩ ሰባክያን እንደ ነበሩና እንደአሉ የታመነ ነው ። ይሁን እንጂ ሰባክያን የክርስቶስን ቃል በልበ ምዕመናን እየዘሩ ከጥፋት ወደ ሕይወት መንገድ እንዲመሩ የሚአደርጉ እውነተኛ ሰባክያን እንደአሉ ሁሉ በአንፃሩም የሰባክያንን ስም የሚያስነቅፉ የስም ሰባክያን እንደሚገኙ ግልጽ ነው በውነቱ ሰባክያን የተለየ ባህርይና አቋም ሊኖራቸው ይገባል ። ምክንያቱም አንድ ሰባኪ የሚሠጠው ትምህርት በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለው በቅድሚያ ሰባኪው ከፉ ስም ከሚአሰጡ አስነቃፊ ተግባሮች ርቆ በቅድስና በመልካም ምግባር ታንፆ በመጥፎ ምግባር የማይገመት እውነተኛና ታማኝ ሰባኪ ሆኖ ሲገኝ ነው ።

ሰባኪው በዚህ አንፃር ተመስርቶና ጸንቶ የክርስቶስን ቃል ካስተማረ ትምህርቱ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ኑሮት ብዙ ሰዎችን ከጥፋት ወደ ሕይወት ለመመለስ ይችላል ። በተለይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መጥፎ ሰባክያን ሲገልጽ እንደዚህ ብሏል በጢሞቴዎስ በም ፩ በቁ.፭ ላይ የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንፁህ ልብና ከበጐ ሕሊናዊ ግብዝንት ከሌለበት ዕምነት የሚወጣ ፍቅር ነው ። ከእነዚህም አንዳንዶች ስተው የሚሉትን ወይም ስለእነርሱ አስረግጠው የሚናገሩትን ሳያስተውሉ የሕግ አስተማሪዎች ሊሆኑ እየወደዱ ወደ ከንቱ ንግግር ፈቀቅ ብለዋል ። ይላል እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አባባል አንዳንድ ሰባኪዎች በቅድሚያ እራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሳያስገዙ ለጥቅም ብቻ ሲሉ በሰባኪነት ተመድበው ወንጌልን ለምዕመናን ሲሰብኩ ቆይተው በኋላ በአልሆነ ቦታ ተሰማርተው ሲታዩ በምዕመናን ዘንድ ተቀባይነትን ያጣሉ ። ይህ ከሆነ ከመጥፎ ሰባክያን መልካም ሰባክያንን ለይቶ በስብከት ስራ መመደቡ የሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ሊሆን ይገባል እንላለን።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አሁንም በድጋሚ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ በ፩ኛ ጢሞቴዎስ በም.፮ በቁ.፳ ላይ ጢሞቴዎስ ሆይ በውሼት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና ከመከራከር እየራቅህ የተሠጠህን አደራ ጠብቅ ይህ እውነት አለን ብለው አንዳንዶች ስለ ዕምነት ስተዋልና በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ መክሮታል ። አንድ ሰባኪም ለዓለም ከሚመች በከንቱ መለፍለፍና መከራከር ዕርቆ ንፁሑን የእግዚአብሔር ቃል በንፁሕ እንደበት መስበክ ይኖርበታል ። እንዲሁም ሰባኪው እውነትን የሚናገር በአንደበቱ የማይሸነግል በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ ጽድቅን የሚአደርግ በቅንነት የሚሄድ እውነተኛ ሰባኪ ከሆን ተወዳጅነቱ በሰዎች ውስጠ ልቡና ለዘለዓለም ተቀርፆ ይኖራል ። እንዲሁም ሰባኪው ሰው ለሰው ምንና ምን መሥራት እንደሚገባው አስቀድሞ ማወቅ ይኖርበታል ። ይህን ከተረዳ ለሰዎች በሚአቀርበው ትምህርትም ችግር ሊፈጥርበት አይችልም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ከዚሁምዕራፍ በቁጥር ፲፩ ላይ አንተ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከዚህ ሽሽ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል ዕምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታትል መልካም የዕምነትን ገድልን ተጋደል የተጠራህለትን ም በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘለዓለም ሕይዎት ያዝ በማለት ምክርና ማፅናኛ የሚሆን ቃል ጽፎለታል ። ሐዋርያው የጻፈው መልእክት ለጢሞቴዎስ ብቻ ሳይሆን እስከ አሁን ለሚገኙ ሰባክያን ለወደፊትም ለሚነሱ ጭምር በቂ ምክርና አጽናኝ ሊሆናቸው ይችላል ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ በስም ሰባክያን የሆኑ ምንነታቸውን ሳያውቁና ከላይ የተጠቀሱትን ቃሎች ሳይገነዘቡ ንፁሑን የእግዚአብሔርን ቃል እንክርዳድ ከሆነ ከመጥፎ ቃል ጋር ቀላቅለው በማስተማራቸው የእውነተኛ ሰባክያንን ስም በከንቱ ነገር ሲአስጠሉ ይታያሉ ። ታዲያ ንፁሕ ስንዴ ካልተዘራ እንክርዳድ ተቀላቅሎ መብቀሉ ስለማይቀር ገበሬው ንፁሕ ፍሬ እንዲያገኝ ስንዴውን ከመዝራቱ በፊት እንክርዳዱን አስቀድሞ መለየት አለበት ። በአንፃሩም በጅምላ ሰዎችን ለወንጌል ሥራ መመደብ ሳይሆን ለወንጌል አገልግሎት የሚገቡትን ሰዎች መርጦ ሰባክያን እንዲሆኑ ቢደረግ በውነቱ ሥራው ከመቃናቱም በላይ የስብከቱም አሰጣጥ በምዕመናን ዘንድ መልክ ኖሮት ከፍተኛ ውጤት ሊታይበት ይችላል ። እንግዲህ ጥሩ ሰባክያንን መርጦ ማሠማራቱ አሁን ኃላፊነት ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ቢሆን ጥሩ ነው እንላለን ።

ስለመጥፎ ሰባክያን በትንቢተ ኢሳኢያስ በም. ፳፰ በቁ.፮-፰ ባለው ቃል ሲገልጽ እነዚህ ደግሞ ከወይን ጠጅ የተነሳ ይስታሉ ከሚአስክርም መጠጥ የተነሳ ይፋንናሉ ካህኑና ነቢዩ ከሚአስክር መጠጥ የተነሳ ይስታሉ በፍዳም ይሰናከላሉ በራእይ ይስታሉ ማዕዱ ሁሉ ጥፋትን ርኩስነትን ትሞልቷል ንፁህ ሥፍራ እንኳ የለም ይላል እንግዲህ ይህ አባባል የሚመለከተው ከቅድስና እርቀው የወይን ጠጅ ለመጠጣት የሚጐመጁትን እንጂ ) በቅድስና ፀንተው ስለክርስቶስ በውነት የሚሰብኩትን ወንጌላውያንን አይመለከትም ።

እኛም ይህንን የጠቀስነው ያለምክንያት ሳይሆን ምክንያት አለው ምክንያቱም አንድ ቁስል ካልፈረጠ ወይም በሕክምና ካልዳነ ቁስሉ ሰውነትን ከመጉዳት አልፎ እስከ ሕይወት ማጥፋት ይደርሳልና እንዲሁም በያዕቆብ መልእክት በም.፩ በቁ.፳፮ እስከ ፍጻሜ እንዲህ በማለት ይገልጻል አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚአመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የዕርሱ አምልኮ ከንቱ ነው ። ንፁሕ የሆነ ነውር የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ በዓለም ከሚገኝ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው ይላል ። አንድ ሰባኪም እንደ ቃሉ አባባል በዓለም ከሚመች እድፍና አንደበትን ከሚአስት መጥፎ ተግባር ርቆ ወንጌልን ቢአስተምር ከእግዚአብሔር ዘንድ ቅድስናን ያገኛል ። ነገር ግን አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ የእግዚአብሔርን ቃል የሚመሰክር ከሆነ የእሳት ፍሕም በራስ ላይ እንደማድረግ ያለ ነው ።

ስለዚህ ሰባክያን አንደበትን ከሚአስቱ ዓላማን ከሚአበላሹ ነገሮች መራቅ ለወንጌል አገልግሎታቸው በቂ ማስረጃ ሊሆናቸው ይችላል ። ከዚህም ሌላ ደግሞ ሰባክያን ወንጌልን በሚሰብኩበት ጊዜ አንዳንድ ችግር እንደሚገጥማቸው እሙን ነው ከችግሩም አንዱ በየወር በዓሉ ወንጌልን ለማስተማር በሚጀምሩበት ጊዜ ማሕሌቱ አላለቀም ወይም ማሕሌት አይቋረጥም በማለት ወንጌልን ተምረው መሄድ የሚገባቸው ምዕመናን ሳይማሩ ይሄዳሉ በውነቱ ከሆነ ማሕሌቱም ሆነ ስብከቱ ያው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑ የታመነ ነው ። ይሁን እንጂ ለሁሉም ጊዜ አለው እንደተባለው ሁሉ ለማሕሌቱና ለስብከቱ ጊዜ ተሰጥቷቸው ማሕሌቱም በጊዜው ስብከቱም በጊዜው ሆኖ የወንጌል ትምህርት ለምዕመናን በወቅቱ ቢሰጥ አስፈላጊ መሆኑን እየጠቆምን በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙ አስተዳዳሪዎች በዚህ ቅዱስ ዓላማ ቢተባበሩ መልካም መሆኑን እንጠቁማለን ።

ይህ ከሆነ መምህራንም ሆኑ ሰባክያን ያንዲት ቤተ ክርስቲያን ልጆች እንደመሆናቸው መጠን ስብከቱም ሆነ ማሕሌቱ ለራሳችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ስለሆነ ሳይነቃቀፉ ማሕሌቱም ሆነ ስብከቱ በየተራ ቢፈፀሙ ለቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አንድነት ጠቃሚ መሆኑ አያጠራጥርም ።

በአጠቃላይ የስብከት ሥራ እንደ ቀላል የሚቆጠር ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን ሥራ የመጀመሪያው ነው ። ምክንያቱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ ፲ በቁ.፳ ላይ እንዲህ ይላል እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው አዘዛቸውም እንዲህም አለ በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ ወደ ሳምራውያን ከተማ አትግቡ ይልቅስ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ የሚል ቃል ተናግሮአቸዋል ።

ስለዚህ ሰባክያን ያላመኑትን የሚአሳምኑ ያመኑትን የሚአፀኑ ያልተጠመቁትን አጥምቀው ከእግዚአብሔር ልጅነት የሚአሰጡ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስለሆኑ አገልግሎታቸው ከፍተኛ ግምት የሚሠጠው እንጂ እንደ ቀላል ሥራ የማይቆጠር አለመሆኑን ሁሉ ሊያውቀውና ሊረዳው ይገባል ።

መሪጌታ ተሰማ ገ/ሚካኤል





www.ethiopianorthodox.org

# ቅድ ....

ከዝ፡ ፲፭ የዞረ

ለዱትም ሰማይ ፀሐይን አወጣች ሲል ደራሲው ጽፏል ።

እንግዲህ መልካም ሥራ መስራት ራስን ብቻ ሳይሆን ወገንንም ይጠቅማል ከፉ ሥራ መሥራትም መጥፎ ውጤትን አስከትሎ እራስንና ወገንን ሃገርንም ሳይቀር የሚጐዳ ይሆናል ። ቅድስት ሃና ግን ከላይ ታሪኳን ባጭሩ እንደተመለከትነው እግዚአብሔርን ፈሪ ሰውን አክባሪ ምንም እንኳ ልጅ ባለመውለዷ ብታዝንም ከቤተ እግዚአብሔርና ከጸሎት ያልራቀች ጻድቅት ሴት እንደ ነበረች እንጂበጊዜአችን እንደሚፈፀመው ልጅ አጣሁ ለምን ይሆን?'' እወቁልኝ ብላ አባይ ጠንቋይ ቤት ያልሄደች ከዛር ኪቃልቻ ቤት ያልሰገደች ሴትናት በዚህም ሥራዋ የዓለምን መድህን አስገኝ የምትሆነውን እመቤታችንን አስገኝችልን ራሷ ተጠቅማ ለዓለሙም ተረፈች ።

ስለዚህ እኛም የእናታችን የቅድስት ሃናን አርአያ በመከተል ጥሩ እንሥራ ሥራ ለሰሪው እሾህ ለአጣሪው ተብሏል ና የቤተ ክርስቲያችን መጽሐፍ ስለ ቅ/ሃና ሲገልጽ ኅዳር ፲፭ ቀን የጻድቅት ሃና የእረፍቷ መታሰቢያ ቀን ነው እንግዲህ ሁላችንም በታላቅ ትህትና በአኗን እንድናከብረው ያስፈልጋል በተለይም የሴቶች ልጆች መመኪያ የሆነችውን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አስገኝታልናለችና ልናከብራት ይገባል ።

ብርሃን ተድላ



በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ ስለአንተ መላእክቱን ያዝዛልና በእጆቻቸውም ያነሡሃል እግርህ በደንጊያ እንዳይሰናከል

መዝሙር ፺፩ . ፲፩

# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፣

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፣

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየ ተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org